From - [illegible]
to Sharon.
28th of May
2007.

*ማስታወቂያ*

ይህ መጽሐፍ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 1964 ዓ.ም ተጽፎ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1990 ዓ.ም የማተም መብት ከደራሲው ስለተሰጠን እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1992 ዓ.ም የዚህ መጽሐፍ ባለቤትነት በሕግ የታሰረ ለመሆኑ ልናስታውቅ እንወዳለን.

አታሚ ድርጅት

*ይህ መጽሐፍ ለአያቴ ለአለቃ
አማኔ ቦጋለ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ተጻፈ።*

## መግቢያ

በ570 ዓ.ም የተነሳው ሙሐመድ ያቋቋመው የእስልምና ሃይማኖት በዓለም በሞላ በተስራጨበት ጊዜ የኛ አሕጉር የሆነችውን አፍሪካን ሊያዳርሳት ምንም ያህል አልቀረውም ነበር ።

የክርስቲያን ደሴት እየተባለች የምትጠራውን አገራችን ኢትዮጵያንም በየጊዜው የምስር ፣ የቱርክና የየመን አረቦች በየአቅጣጫው እየገቡ የኢትዮጵያን ምስራቅና ሰሜንምእራብንም ሜዳማውን ቆላማ ቀበሌ የዘላኑን መኖሪያ በትምህርታቸው አዳረሱት ። ከዚያም አልፈው የወሎን ግዛት ደጋማ ቀበሌ በሙሉ የእስልምና ሃይማኖት አስራጩበት ። ይኼ የእስልምና ሃይማኖት በተለይ ግራኝ ሙሐመድ ኢትዮጵያን ለአስራአምስት አመታት በገዛበት ጊዜ በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ስለተዳረሰ በወቅቱ ለነበሩት የኢትዮጵያ መሪወች ብዙ ጊዜ ለአስተዳደራቸው ብርቱ እንቅፋት ሲፈጥርባቸው ስለነበር በመጀመርያ አፄ ቴወድርስ በኋላም አፄ ዮሀንስ እስላሞችን ክርስትና እንዲነሱ ለማድረግ ሞክረው ነበር ። ይህም ችግርን እንጅ እንደታሰበው መልካም ውጤት አልሰጠም ነበር ። ዳሩ ግን ሁሉን የሚችል አምላክ ከእስላሞች መካከል ሸህ ዘካርያስን አስነስቶ ለባለስልጣኖቹ ከባድ የነበረውን ተግባር የሚያቃልል ታላቅ የታሪክ ምዕራፍ ተከፈተ ። ይህም ታሪክ መለኮታዊ ስልጣን የተዋሐደው በመሆኑ ወንድማማቹን ሕዝብ ከማቀራረቡ በቀር ያልታወቀውን ሚስጥር ለማዎቅ ሰላምንና ፍቅርን ለማግኘት አምላክ ያቀደው ነበር ።

## ማውጫ

### ምእራፍ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 - | የዘካርያስ ልደትና እድገት ..................... | 1 |
| 2 - | ዘካርያስ በትምህርት ቤት ......................... | 3 |
| 3 - | የዘካርያስ ጋብቻ .................................... | 6 |
| 4 - | የሸህ ዘካርያስ እራእይ ............................ | 15 |
| 5 - | የሸህ ዘካርያስ ጉዞ ................................ | 19 |
| 6 - | ሸህ ዘካርያስ የተጠሩበትን ስራ መጀመር ....... | 23 |
| 7 - | ችግሩን ለማቃለል የተገኘ ዘዴ ................. | 34 |
| 8 - | የመጀመርያው ክስ ............................... | 37 |
| 9 - | የወርቅነህ ሙሐመድ ሞት ....................... | 52 |
| 10 - | እድዋ ላይ የተጀመረው ስራ ..................... | 60 |
| 11 - | ወደ በጌምድር ጉዞ ................................. | 66 |
| 12 - | የሸህ ዘካርያስ ክራስ ጉግሳ ላይ መከሰስ ......... | 76 |
| 13 - | ይግባኝ ወደ እዲስ አበባ ........................ | 83 |
| 14 - | ታላቁ ጉባኤ ........................................ | 86 |
| 15 - | እዲስ ክሳሽ ........................................ | 100 |
| 16 - | ወደመካ እንዲሳኩ መጠየቅ ................. | 110 |
| 17 - | የመልስ ጉዞ ....................................... | 113 |
| 18 - | የእለቃ ንዋየክርስቶስ መጠመቅ ............ | 116 |
| 19 - | የመጨረሻ ምክር ............................. | 142 |


## ምዕራፍ 1

## የዘካርያስ ልደትና እድገት

የሸህ ዘካርያስ አባት አቶ ጅብሪል ከአባታቸው ጋር በበጌምድር ጠቅላይ ግዛት በጋይንት አውራጃ በነገላ ቀበሌ እውሽንድባ ከተባለ ቦታ ይኖሩ ነበር ። ለአቅመ አዳም በደረሱ ጊዜ የእድሜ ጓደኛ የምትሆናቸውን ለመፈለግ ከቦታ ወደ ቦታ በሚዘዋወሩበት ጊዜ ከጉና ተራራ በስተ ደቡብ ምክሬ ከተባለ ቦታ ዘመድ ለመጠየቅ እስመስለው ሄደው ሳል እንዲት የተዋበች ቆንጆ ስሟ በፍታ የተባለች ልጅ በእይናቸው ስለገባች በፍቅር ተለከፉ ። በፍቅር በመለከፋቸው አነድ ችግር ተፈጠረ ። ችግሩም እሳቸው እስላም ሲሆኑ ልጅቷ ክርስትያን መሆኗ ነበረ ። ይሁን እንጅ ጅብሪል የተወጋበት የፍቅር ጦር የበፍታንም ስሜት ክፉኛ ጎድቶት ኑሮ የበሰለ ብርቱካን የመሰለችው በፍታ ጅብሪል ሲገባና ሲወጣ ሳታስበው ዓይኗ እየተወረወረ ለጉብዝናው ይህ ጎደለው የማይባለው ጅብሪል መፍትሄ የማይገኝለት በሽታ ወደቀበት ይህም ህመም ተሳሳፊ ስለሆነ በፍታም አብራ ስለተሰቃየችበት ነጠላዋን እንስታ በገበያ እመካኝታ ሳሊ ገበያ ስትሄድ ጅብሪል ተከትሎ ስለጠለፋት ተያይዘው ጋይንትን እቋርጠው ነገላ ወርደው እውሽን ድባ ከተባለው መንደር የጋብቻ በዓላቸውን በማክበር ስርጋቸውን እስረጉ ።

ይህም የጋብቻ ስነስርእት የተፈጸመው በፍታ የራሷን ሐይማኖት ትታ የባሏን ሐይማኖት ተቀብላ ነበር ። አቶ ጅብሪል የሚተዳደሩበት ስራ በእርሻና በንግድ ነበር በተጨማሪም ከብት ለማርባትና ንብ ለማነብ ቦታቸው ተስማሚ ስለነበር ሁሉ ነገር ከዛው ከቤታቸው ይገኝ ነበር ። ነጭ ጤፍ በጎተራ፣ ወፋፍራም ሙክት፣ ሻኛማ በሬ፣ ወተታም ላምና ዳንዴ በቅሎ በበረታቸው የሚገኘው አቶ ጅብሪል ከወይዘሮ በፍታ

ጋር የነበራቸው ፍቅር የተሟላ እንዲሆን ለወደፊት ስፈ. ታሪክ ባለው ወንድ ልጅ በ 1837 ዓ.ም ተበከሩና ስም ለማውጣት አባትና እናት ሲሽቀዳደሙ አባትየው ዘካርያ እለዋለሁ ሲሉ እናቲቱ ደግሞ ይበሉ ባይሆን ዘካርያስ ይባል በማለት ምንጊዜም በሀሳብ የማይራራቁት ባልና ሚስት በስም ማውጣቱ ጉዳይ ከስምምነት ደረሱ ።

ይህ የታደለ ትዳር በተከታታይ ሌሎች ሁለት ወንድ ልጆችና አንዲት ሴት ልጅ ስለታከሉበት የዘካርያስን ተከታይ ዋሴ ሌላውን ይሳ (ኢየሱስ) ሴቷን እሕሊቱ ብለው ስየሟቸው ። ስለሙያቸው ጉዳይ የበሀሩን ዘካርያስን የቁርአን ተማሪ ዋሴን ነጋዴ ይሳን ገበሬ እህሊቱን የናቷን የቤት ሙያ አስተምረው ሲያስማሯቸው ሁሉም በየዋሉበት አስደሳች ሲሆኑ ዘካርያስ ግን ባለስፈ ታሪክ ሆነ ።



## ምዕራፍ 2

## ዘካርያስ በትምህርት ቤት

ዘካርያስ እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሱ አባታቸው አቶ ጀብሪል በአካባቢው ወደ ነበሩት አስተማሪ ሽህ ውመር ወስደው እንዲያስተምሩላቸው ስለጠየቋቸው ሽህ ውመርም ጥያቄውን ተቀብለው ጊዜው በሚፈቅደው መንገድ ዘካርያስን ማስተማር ጀመሩ ። ዘካርያስ በትምህርት ቤት የሚማሩበት መጻህፍት በጣም አነስተኛ ነበር እንዲያውም የዋንዛውን እንጨት ለስለስ አድርገው ጠርበው ለመምህራቸው ሲያቀርቡ ሽህ ውመር ከለስለሰው የዋንዛ እንጨት ላይ የአርብኛውን ፊደል በጋለ ቀጭን ብረት እየቀረጹ ሲስጡዋቸው አእምሯቸው ለትምህርት እጅግ በጣም የጠራው ዘካርያስ ወዲያው በጥቂት ጊዜ ውስጥ የፊደሎቹን ጠባይ በማስተዋል ስላከናወኑ በመምህራቸው በሽህ ውመር ፊት ዘካርያስ ማን መሆናቸውን እንዳስመስከሩ አራሳቸው ሽህ ውመር መስክረውላቸዋል ይባላል ። ከፊደሉ አልፈው ቁርአን መቅራት የጀመሩት ዘካርያስ የቁርአኑን ትርጉም ሲጠይቁ መምህራቸውን እስከሚያስቆጣ መድረስ ጀመረ ። ቢሆንም ዘካርያስ በትምህርት ወደ ፊት ለመግፋት ሰፋ ያለ አስተያየት ያላቸው ሰው ስለነበሩ በትእግስት የቁርአንን ትርጉም ሲያጠኑ አሪቱ ፤ መዝሙሩና ትንቢት ወንጌልም ጭምር ብለው ጠየቁ ተሁረት ዘቡርና ኤንጅል ከሰማይ ከወረዱ እንደሚያዙት ልንኖር አይገባንምን ? ብለው ሽህ ውመርን ቢጠይቋቸው አንተን ኢልም ተፍላፊ ማነው የሾመህ ብለው በተማሪ ቤት ባሉበት ጊዜ በጥፊ እንደመቷቸው ለአለቃ ብርሌ ደስታ ነግረዋቸው ስለ ነበር አለቃ ብርሌ ደስታ ለኔ አጫውቱኝ ። ይህንና ይህን የመሰሉ ጉዳዮች ሁሉ ቢደርስባቸውም እንኳን የመምህራቸውን ፤ የጓደኞቻቸውንና ከራሳቸው በታች የሚተዳደሩትን ተማሪዎቻቸውን እንኳ በታላቅ ትግስት

እየተመለከቱ የሚተዳደሩትና የሚያስተዳደሩት ዘካርያስ ይህችን ጥፊ ከትምህርት ቆጥረው ወደፊት ለሚገጥማቸው ችግር ትግስት የሚያሻቸው መሆኑን ተገንዝበው ትምህርታቸውን ቀጠሉ ። በሚማሩበት ወቅት በተማሮች መካከል ከፍ ያለ ብልጫ ይታይባቸው ስለ ነበር በቅናት መንፈስ ከመምህራቸው ጋር እንዲጋጩ በነገረ ሥራ ለማጣላት ቢሞክሩም እስተዋይ አእምሮ ከደግነት ጋር የታደሉት ዘካርያስ በትግስትና በርጋታ የሚከሰሱበት ጉዳይ ሁሉ ሀሰት ለመሆኑ መልካሙ ጸባያቸው በመምህራቸው ፊት ተቃዋሚወችን ያጋልጣቸው ስለነበር ተግባራቸው ውድቅ ይሆንባቸው ነበር ። ይህም ሌላው የትግስት መለማመጃቸው ነበር።

ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ጊዜ መምህራቸው ከማስተማር በቀር ምንም የሚተዳደሩበት ስላልነበራቸው አገር ላገር በመቄት ፤ በሸድሁ ፤ በጋይንት ፤ በፋርጣ ፤ በመልዛ በብናት ፤ በበለሳና በሊቦ እየተዘዋወሩ የአርብኛውን ፊደል በልዩ ልዩ መሳርያ በእንጨት ፤ በብራናና በክርታስ ወረቀት እየጻፉ በመሸጥና እንዲሁም የአረብኛ ንባብ መልመጃ እየጻፉ በመሸጥ ማንንም እርዳታ ሳይጠይቁ እራሳቸውን ደግፈው ትምህራታቸውን ፈጽመው ለመምህርነት የሚደርሱበት ጊዜ እየተቃረበ ሄደ ። ከዚህ በላይ በዘረዘርኳቸው ቦታወች ይዛወሩ የነበሩ መምህራቸው ሸህ ውመር በነዚህ ቦታወች እየተዘዋወሩ ያስተምሩ ስለነበር ነው ።

ዘካርያስ እንዳንድ ጊዜ ወደ ነገላ ወደ ወላጆቻቸው ለጉብኝት ሲመጡ መምህራቸውን ሸህ ውመርንና የተማሪ ጓደኞቻቸውን ጭምር ይዘው ስለሚመጡ አባታቸው እቶ ጀብሪል እና ወንድሞቻቸው እቶ ዋሴና እቶ ይሳ በደስታ ተቀብለው ሙክት እያረዱ ማር



እየበረዙ የነገላን ነጭ ጤፍ የማር ሰፈፍ የመሰለ እንጀራ በሙክት መረቅ እየፈተፈቱ ሲያቀርቡላቸው ይህን የተጋበዙ መምህራቸውና ጓደኞቻቸው ከዚህ የሞቀና የደመቀ ቤታቸው ወጥተው በሸቀጥ ቆሎና በዙረት የቅልውጥ እንጀራ በታማኝነትና በትጋት በትምህርታቸው ከሁሉ በላይ መሆናቸውን ሲመለከቱ ስለ ትእግስታቸውና ለወደፊቱ ታላቅ ተስፋ ሊጣልባቸው የሚቻል ልዩ ሰው መሆናቸውን ላባታቸውና ለወንድሞቻቸው ይገልጹላቸው ነበር ። ዘካርያስም ይህን ሲሰሙ ኩራትና ትእቢት ሳይሰማቸው ለተፈለጉበት ተግባር ብቁ የሚያደርጋቸውን ጸባይ ስለሚከታተሉ በሚዛወሩበት ቦታ ሁሉ ብልጫቸው በጉልህ በመታየቱ ሸህ ዘካርያስ እየተባሉ ይጠሩ ጀመር ። ከመምህራቸው ነጠል ብለው በሚጓዙበት ጊዜ የሸህ ውመር ተማሪ ከሶስት ሁለት እጅ ሸህ ዘካርያስን በመከተሉ በቁርአን ሊቅነታቸውን አስመሰከሩ ። ይሁን እንጅ ሸህ ዘካርያስ መምህራቸውን ሸህ ውመርን ያባት ያህል እያከበሩ ሌሎች ተማሪወች እንዲያከብሯቸው በማሳየት ምሳሌ ስለሆኑ ሸህ ውመር በጣም ይወዷቸው ነበር ። እንዲያውም የቁርአኑን ትርጉም ሲጠይቋቸው ዘካርያስን ጠይቁት እያሉ ያስቸገራቸውን ጥያቄ እንዲያብራሩላቸው ይልኳቸው ነበር ። ሸህ ዘካርያስም እንደመምህራቸው በጥፊ ከመማታት ይልቅ ከተማሪያቸው ጋር በመመካከር ለጥያቄው የተሻለ ትርጉም በመተባበር ፈልገው ለመረዳትና ለማስረዳት መፍትሄውን ያገኙለት ነበር ።

## ምዕራፍ 3

## የዘካርያስ ጋብቻ

በእውቀትና በቁመት ያደጉት ሸህ ዘካርያስ የእድሜ ጓደኛ የምትሆን ሚስት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ደጉ እባታቸው አቶ ጅብሪል ስለተገነዘቡ እንደ ጊዜው ልማድ ለልጃቸው ለሸህ ዘካርያስ ስለ አዋቂአቸው እባቴ የሚያመጡልኝን ሚስት በታዛዥነት እቀበላለሁ ብለው ስለመለሱ ቆላ እብናት በተባለው አካባቢ ሸለግ ቀበሌ የሚኖሩትን አዛውንት የመክሬ ዘይኑን ልጅ እስያ መክሬን እጋቡዋቸው ። ስለ መክሬ ዘይኑ የሚነገረው

ባገሬ ቢሆን በነ መክሬ !
እንጠግባለን ሲታረድ በሬ ።

እያሉ ድሆች ይናገሩላቸዋል ። (ይዘም ህብታም ነበሩ ለማለት ነው)

ዘካርያስ የመጀመርያ ሚስታቸው እስያ መክሬ አንድ ወንድ ልጅና ሁለት ሴት ልጆችን ወልደው ስለሞቱባቸው ሁለተኛ አግብተው አንዲት ሴት ልጅ ወልደዋል ። በመጨረሻም ወይዘሮ አማረች ለምለም የተባሉትን አግብተው እስከ እለተሞታቸው አብረው ኑረዋል ። ወይዘሮ አማረች መካን ስለነበሩ አልወለዱም ዳሩ ግን ሸህ ዘካርያስ መንግስት ያወቃቸው ታላቅ ሰው በመሆናቸው ወይዘሮ አማረች እንግዳ በመቀበልና በቤት አያያዝ በጣም የታወቁ ወይዘሮ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል ። እኒህ ወይዘሮ ከህይወታቸው ወደ መጨረሻው ክፍል ሲጠነቀቁላቸው ከነበሩት መካከል አንዱ ስለነበርኩ ያለቃ ዘካርያስን ታሪክ በሰፊው ካስረዱኝ መካከል አንዷ እሳቸው ነበሩ ። ወይዘሮ አማረች ምንም እንኳ የትውልድ አገራቸው በለሳ ቢሆንም ከሸህ ዘካርያስ ጋር ለመተዋወቅና ለጋብቻ የበቁት ሸህ ዘካርያስ በሃይማኖት ተከለው ከእስላሞች ጋር በሚከራከሩበት ጊዜ ታናሽ ወንድማቸው ዋሴ ለምለም ከሸህ ዘካርያስ ደጋፊወች



አንዱ በመሆን አብረው ወደ ሰቆጣ ሄደው ስለነበርና ሰፈርተኞቹን ስንቅ በማቀበል ሲረዱ ስለተዋወቁ በጠባይና በሙያ እጅግ የተመሰገኑ ወይዘሮ አማርች ለምለም ታሪካቸው በንጉሠ ነገሥቱ መንግስት የተመሰገነውን አለቃ ዘካርያስን በሕግ አግብተው በብዙ መቶ የሚቆጠረውን ተማሪያቸውን በብዙ ሽህ የሚቆጠረውን ተከታያቸውን እንዲሁም በመቶ የሚቆጠሩትን ጓደኞቻቸውንና ደጋፊወቻቸውን በተመሰገነ አኳኋን እየተቀበሉ በመሸኘት ግሩም የሆነ እርዳታቸውን ለተከበሩ ባለቤታቸው አበርክተዋል ።

ሸህ ዘካርያስ የመጀመሪያ ሚስታቸውን እንዳገቡ በኃይንት አውራጃ ነገላ አንባ እስላም ተቀምጠው በብዙ መቶ ለሚቆጠረው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ለሆነው ሕዝብ ያደጉበትንና በብዙ ድካም የገበዩትን እውቀት ለማስተማር ይዘጋጁ ነበር ። ሸህ ዘካርያስ በዝግጅታቸው ጊዜ በአእምሯቸው የሚወጣና የሚወርድ ከብዙ ችግር ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1. የናታቸው ወገኖች
2. አፄ ቴወድሮስ እስላሞች ክርስትና እንዲነሱ መፈለጋቸው
3. አፄ ዮሐንስ በአዋጅ እስላም ሁሉ ክርስትና እንዲነሳ ማስነገራቸው

ይህንና ይህን የመሳሰሉት ጉዳዮች አስቸጋሪ ቢሆንባቸውም ሸህ ዘካርያስ ከህጻንነታቸው ጀምረው በቁርአን ቃል ሰልጥነው ያደጉትን ለማስተማር መሞከራቸው አልቀረም ። በዚህ ጊዜ የናታቸው ወገኖች አሁን የህታችን ልጅ እስላሙን ሁሉ ክርስትና

ሊያስነሳ ይችላል እያሉ ለአፄ ቴወድሮስ ሹማምንት ሲያዋዩዋቸው በልመናም በስልጣንም ወደ ክርስትና እንዲመለሱ የሃይማኖት ባለስልጣኖች ሸህ ዘካርያን ያስቸግሯቸው ነበር ምክንያቱም አፄ ቴወድሮስ ቱርኮች በመተማ በኩል እየመጡ በእስልምና ሃይማኖት እያታለሉ ቅኝ አገር ለማስፋፋት አገሩን ቀምተው ተገኘ ሲያደርጉት ሲያታልሉት ስለተመለከቱ ከዚህ በላይ የተማሩት የቤተክህነት ትምህርት እስልምናን ስለሚነቅፍ በእስልምና ሃይማኖት የሚመራውን የቱርክ መንግስት አጥብቀው ስለሚጠሉ ገና ልጅ ካሳ በሚባሉበት ጊዜ አስራ ስድስት ሽህ ጦር አስከትለው የቱርክን መንግሥት ለመዋጋት ወደ ሱዳን ገዳሪፍ ወረዱ ። ገዳሪፍ እንደደረሱ የቱርክ መንግሥት በኢትዮጵያ ምዕራብ የሚኖረውን በጠረፍ ያለውን ኢትዮጵያዊ በእስልምና ሃይማኖት እያሳመኑ በሚነሳባቸው ባላጋራ መከላከያ የሰለጠነ የጦር ሠርዊት በስተኋላቸው ደብቀው ይጠባበቁ ስለ ነበር በተደረገው ጦርነት እራሳቸው ከመቁሰላቸውም በላይ ሠራዊታቸው በጣም ተጎድቶባቸው ስለ ነበር በእስላሞች ላይ የከፋ ጥላቻ ስላደረባቸው በኋላም ሙሉ ስልጣን በያዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ዙሪያ የሚገኘውን በቆላው አገር የሰፈረውን ሕዝብ በእስልምና ሃይማኖት ያመነ መሆኑን ስላወቁ እስቀድመው በአፄ ልብነድንግል የደረሰውን በታሪክ የተከታተሉ ብልሁ ንጉሥ አፄ ቴወድሮስ የእስልምና ሃይማኖት እማኞች የኢትዮጵያ ጠላቶች የሆኑትን ትርኮችንና ምስራውያንን እየሳቡ ከማምጣታቸው በስተቀር ባገር ውስጥ ለሰላምና ጸጥታ ጠንቅ መሆናቸውን ሊረዱባቸው ከቻሉት አንዱ አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሳ ከተባለው መጽሐፍ በገጽ 133 ላይ 'እስላሙ ክርስትያኑን ገደለው' በሚል አርስት የተጻፈውን ከዚህ ቀጥየ አቀርብላችኋለሁ " እንድ



እስላም ሰው ገድለህል ተብሎ ከሸዋ ተይዞ የመጣ ቀረበላቸው ። ንጉሡም ምን በድሎህ ገደልከው ቢሉት ወንድሜን ቢገድልብኝ ነው አላቸው ። ወንድምህን ለመግደሉ በምን ይታወቃል ማስረጃ አለህ ወይ እያሉ ልዩ ልዩ ጥያቄ ሲያደርጉለት በመካከሉ እስላሙ እንስቶ ንጉሥ ሆይ ደሜን በከንቱ አላፈስም የገደልኩበት ምክንያት ካፊርና እስላም ጥንት ከመሐመድ ጀምሮ እስከ ግራኝ ከግራኝ እስከ ዛሬ ድረስ ደመኛ ነን በማለት መግደሉን ስላመነ እሱም በጠበንጃ ሲመታ የሙሐመድ ባርያ ብሎ ፎክሮ የህይወቱ ፍፃሜ ሁነ ።"

በዚህ ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ ከአመዴ በሽር ጋር የተጣላነው በግዛት መስሎኝ ነበር ለካስ በሃይማኖት የተነሳ ደመኞች መሆናችን ነው ጠባችን የከረረ አሉ ።

ይህም አስቀድሞ ከቆሰለው አካላቸው ሌላ ተጨማሪ የልብ ቁስል እንደሆነባቸው አነጋገራቸው ሊያስረዳ ይችላል ።

አፄ ቴወድሮስ አጅግ አጥብቀው ብልህ ሰው ስለነበሩ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመንጠቅ ዋና መሳርያ አድርገው የሚጠቀሙበት የካቶሊክ እና የእስልምና ሃይማኖት እንደሆነ ለመረዳት ስለቻሉ ይህን ለማገድ በነገሱ በስድበተኛው ወር ሐምሌ 8 ቀን 1847 ዓ.ም በደብረታቦር ከተማ 700 ( ሰባት መቶ ) ሊቃውንት በተሰበሰቡበት የሃይማኖት ጉባኤ እንዲሆን ተደረገ ። በውሳኔውም የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን መስረተ አቋም ሲያያዝ የወረደውና የሚታወቀው እርቶዶክስ ተወህዶ ሃይማኖት ነው ። ከዚህ ሃይማኖት ወጥቶ ሌላ ሃይማኖት ሲያስተምር የተገኘ ወይም በሌላ ሃይማኖት የሚያምን ቢኖር የሚቀጣ መሆኑን የጉባኤው ሰብሳቢና አስተማሪው

አቡነ ስላማ አስምተው ተወስነ ። ይህ ውሳኔ እስላሞች እንዳያስተምሩ ጨምሮ የሚከለክል መሆኑ የታወቀ ሲሆን ለወጣቱ ሸህ ዘከርያ የደከሙበትን ትምህርት መና አደረገባቸው ሕግ ተላልፈው ሲያስተምሩ እንዳይገኙ ከባድ ሀላፊነትን የሚያስከትል ሆኖባቸው ነበረ ። ከዚህ የጉባኤ ውሳኔ መታወጅ በኋላ አፄ ቴወድሮስ እስላሞች ወደ ክርስትና እንዲመለሱ ጥሪት እንዲያደርጉ ለምስለኔወቻቸው በጥበብ እንዲሰሩ ይገልጹላቸው ስለነበር በጋይንት ምስለኔ እነ ብላታ ፋሌቅ ወጣቱን ሸህ ዘካሪያስን ከናታቸው ወንድሞች ጋር ሆነው በናታቸው ከክርስትና መምጣት ተጠግተው በስልጣናቸው ተደግፈው በማባበልም ሆነ በግድ ወደ ክርስትና እንዲመለሱ ሙከራ ያደርጉ ነበር ። ሸህ ዘካርያስም በህጻንነታቸው ጀምረው ተምረው ላደጉበት ወግና ልማድ ታማኝ በመሆን እርሳቸውን ክርስቲያን ለማድረግ በግድም ሆነ በማባበል በደረሰባቸው ሙከራ እልተናወጹም ነበር ።

ሸህ ዘካርያ የ 25 አመት ወጣት ሳሉ ከዚህ በላይ የዘረዘርኩት ችግር ቢደርስባቸውም አፄ ቴወድሮስ መቅደላ ከእንግሊዞች ጋር ባደረጉት ጦርነት ባረፉ ጊዜ ይህን ከመሰለ ችግር ነጻ የወጣሁ መስሏቸው ነበር ዳሩ ግን ጥቂት ቆይቶ የከፋ ችግር ደረሰባቸው ።

አፄ ዮሐንስ ከግብጽ መንግሥት ጋራ የነበራቸው ጥላቻ ከአፄ ቴወድሮስ የባሰ ነበር ። ምክንያቱም የግብጽ መንግሥት ግዛቱን ከግብጽ አንስቶ ከሱዳን ጋር ኢትዮጵያንም ጨምሮ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ለማድረስ ያስብ ስለነበር ጦሩን አስከትቶ በመምጣት በ1866 እስከ



1868 ዓ.ም ከባድ ጦርነት አድርገው ከመለሱት በኋላ በግዛታቸው ውስጥ ያሉ እስላሞች ቱርክንና ግብጽን እየሳቡ እያመጡ ለዚህ ሁሉ ንፁህ ደም መፋሰስ ምክንያት መሆናቸውን ከመረዳታቸውም በላይ ለወደፊቱ አስጊነታቸው ስለተረጋገጠ ንጉሠ ነገሥቱ የእስልምናን ሃይማኖት በግዛታቸው ውስጥ ለማገድ አሰቡ ። በዚህ አጋጣሚ ሚስዮናውያንንም ከሀገረቸው አስወጥተው ለማባረር ያሰቡት ሕዝባቸው በሃይማኖት እርስ በእርሱ ሲለያይ አገር የተለያየ ይሆናል ሲሉ ሚስዮናዊያኑ ከኢትዮጲያ እንዲወጡ ሲያስናብቷቸው እንዲህ አሏቸው " እኔ ያገሬን ሕዝብ የእጅ ስራ ጥበብ የሚያስተምሩ ሰጋጃ ሰራዎች አናጺዎች ነጋዴዎች ብረት ሰራዎች የሆኑ የሆኑትን እቀበላለሁ እንጅ እናንተን አልፈልግምና አገሬን ልቀቁልኝ " ብለው ከኢትዮጵያ አስወጧቸው ።

እንደዚሁም በዚያ ዘመን የነበሩትን ፈላሻወችንና አረማውያንን ይልቁንም እስላሞችን በግድ እያቀረቡ ክርስትያን አደረጓቸው ። ክርስትያን አንሆንም ያሉትን እስላሞች በጭካኔ እየቀጡ አስጨነቋቸው ። በዚህ ጊዜ አያቴ አለቃ ቦጋለ እስላም ስለነበሩ አፄ ዮሐንስ ጎንደር ክፍለሀገር መጥተው በደብረታቦር በቆዩበት ጊዜ የአለቃ ቦጋለ ስም ከክርስትና በፊት ሙሐመድ አማኔ ይባል ስለ ነበር የሚኖሩበትም ሰፍራ በግር የአራት ሰአት እርቀት ያላት እርብ ወንዝ አጠገብ ጉብዳ ከተባለ መንደር ስለነበር እና ሙሐመድ አማኔ ባካባቢው ያሉትን እስላሞች የሚያስግዱ በቁርአን ትምህርት ስልጥነው ካደጉት መካከል አንዱ ስለ ነበሩ ወደ ደብረታቦር እንዲመጡ ጥሪ ደረሳቸው ። እንዲጠሩም ያደረጋቸው አቶ የሱፍ በዚህ ሰፍራ መደብ ከተባለው የሚኖሩት እስላም ባለሟል ከመሆናቸውም በቀር እራሳቸው አፄ ዮሐንስ የክርስትና አባት ሁነው ክርስትና ስላስነሷቸው

ክርስትና እስነስተው ስማቸውን ኪዳነ ማርያም አድርገው ብላታ ብለው ቀሚስ አልብሰው እስላሙን ሁሉ እያስገደዱ ክርስትና እንዲነሳ ትእዛዝ ስለተቀበሉ ብላታ ኪዳነማርያም እነ ሙሐመድ አማኔን አስገድደው ደብረታቦር እንዲሄዱ አደረጓቸው ፡፡

ሙሐመድ አማኔና ባለቤታቸው አባቴን የበህር ልጃቸውን ንጉሤን ይዘው ክርስትና ሊነሱ ደብረታቦር እንደደረሱ በሸህ የሚቆጠር እስላም በደብረታቦር ከተማና ባካባቢው ሰብስበው በወታደር እያስጠበቁ የጥምቀቱ ስነስርአት የሚከናወንበት ጊዜ እየተጠበቀ ሳለ ደብረታቦር በሄዱበት ቀን የሙሐመድ አማኔ ባለቤት ለምለም ዘካርያ በጣም መልከኛ ቆንጆ ስለነበሩ የሚጠመቀውን ሕዝብ ሲጠብቁ የነበሩት ዘበኞች እኔ እወስድ እኔ እወስድ ከባልየው ፊት ተጣሉ ፡፡ የሁለቱ ወታደሮች ጠብ ሚስታቸውን ከመነጠቅ የረዳቸው ሙሐመድ አማኔ ሃይማኖቴን በግድ ለውጥ መባሌ ባይበቃኝ ሚስቴን ሊነጥቁኝ ከከጀሉ የንጉሡን እዋጅ ተላልፌ የሆነው ይሁን ብለው ሌሊቱን ሚስታቸውን ይዘው ከድተው ያራት ቀን መንገድ ተጉዘው የንጉሡ ወታደሮች ከለሉበት በረሀ ቋሊሳ ከተባለው ቀበሌ ሄደው ተቀመጡ ፡፡

ብላታ ኪዳነማርያም በጋይንት አውራጃ የነገላ ምስለኔነት ተሹመው አሁንም እስላሙ ክርስትና እንዲነሳ እያስገደዱ ከነሸህ ዘካርያስ ሰፈር ደረሱና በሸህ ዘካርያስ የሚመራውን እስላም ተገዶ ክርስትና እንዲነሳና እንዲቆርብ ቢጠይቁ ሸህ ዘካርያስ ሃይማኖትን ያህል ነገር ሳንረዳና ህሊናችን ሳይፈቅድልን በግድ ክርስትና ልንነሳ አይገባንም ሲሉ ቢመልሱላቸው አስሬ ደብረታቦር እወስድህና ቅጣት ተቀብለህ በግድ ትነሳለህ



የሚል መልስ አገኙና ከብላታ ኪዳነማርያም ጋር ወደ ደብረታቦር እንዲሄዱ ተነገራቸው ፡፡ ነገላ ከደብረታቦር በግር የሁለት ቀን መንገድ የራቀ ከመሆኑም ከጋይንት ደጋ እስከተከዜ ድረስ ያለው ቁልቁለት የወሎ መንገድ ሲሆን ነገላ የነ ሸህ ዘካርያስ መንደር ከዳገቱ አጋማሽ ነው እንዲሁም ይህ አካባቢ በጣም ወጣ ገባ የሆነ አንጋዳ ስለሆነ በነገላ አካባቢ ያሉት እስላሞች ደብረታቦር እንሄድም ብለው እምቢ ማለታቸውን በሸህ ዘካርያስ አማካኝነት ገለፁላቸው ፡፡ ብላታ ክዳነማርያምም ያላቸውን አቅም ተመልክተው በግድ ለማስገደድ እለመቻላቸውን ስለተረዱ ተጨማሪ ወታደር ለመጠየቅ ደብረታቦር ሄደው ወታደር ተሰጥቷቸው ተመልሰው ወደ ነገላ ቢመጡ በግድ ክርስትና አንቀበልም ያሉት እነሸህ ዘካርያስ ጓዛቸውን ጠቅለው ተከዜን ተሻግረው ደረቅ ጦር ሁነው ጠብቋቸው ፡፡ በሁለቱ መካከል ወድያው በተደረገው ግጭት ሸህ ዘካረያስና አብረዋቸው የነበሩት የነገላ እስለሞች እነብላታ ኪዳነማሪያምን ስላባረሯቸው የነገላ ሰው "አባበግዴ" የሚል ቅጥል ስም ለሸህ ዘካርያስ አወጣላቸው ፡፡ በዚህ ጊዜ የተፎከረላቸው ግጥም እንዲህ ይል ነበር ፡፡

አባ በግዴ ዘልቆ ቢያገሳ ፤
የሸድሆ ሰው ስስት ጊዜ እጅ ነሳ ፤
እየወደቀ እየተነሳ ፡፡

ፎካሪው ይህንን ሲፎክር አቅራሪው ደግሞ ( ሸላዩ ማለት ነው) እንዲህ አያለ ይገጥም ነበር ይባላል ፡፡

ሲናቆ ወንዛችን ተከዜ ወንዛችን ፤
የከፋን ጊዜ የጓዝ ማሸሻችን ፡፡
ጎላጌም ሲናቆም ዞጋና ተከዜ ፤
ለከፋው ወንድ ልጅ ይበቃል ሁልጊዜ ፡፡

እገሬ ሲናቆ ወይ እገሬ ዞጋ ያግድም ያግድም ፤
እንግዳው ብዙ ነው እያረማምድም ።

ሸህ ዘካርያስ እስቀድሞ ባዔ ቴወድሮስ እሁንም ባዔ ዮሐንስ ዘመን በደረሰባቸው ችግር ምክንያት ያደጉበትን የቁርአን ትምህርት ካባት የወረሱትን ልማድ ለማስተማር ባለመቻላቸው በላስታ አውራጃ አይና ቡግና ቀበሌ ጣርና ክተባለች ሸንተረር በተፈጥሮ እቀማመጥ የታጠረች ቦታ ላይ መኖርያ አድርገው ለመቀመጥ ወሰኑ ። ይህችን ጣርና የተባለች ስፍራ የመረጡበት ምክንያት 1ኛ/ የንጉሡ ሠራዊት አግኝቶ ሃይማኖታቸውን በግድ ለውጥ እንዳይላቸው ቦታው በቀላሉ የማይደረስበት በመሆኑ ። 2ኛ/ ይህች ቦታ የባለቤታቸው የወይዘሮ እስያ ምክሬ እርስት በመሆኗ ነበር ።



## ምዕራፍ 4

## የሸህ ዘካርያስ ራእይ

ሸህ ዘካርያስ በእርሻና በንግድ እየተዳደሩ ከወንድሞቻቸው ጋር ጣርና ከተባለችው መንደር ሲኖሩ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት ወደ መጨረሻው ስለ እስልምና ሃይማኖት እውነተኛነት በጥብቅ መመርመር ጀመሩ ። ዘወትርም በግል ጸሎታቸው ፈጣሪን በንጹህ ህሊና በእውነተኛ መንገድ እንዲመራቸው በትግስት ለመኑት ። እምላክም የለመኑትን የማይነሳ ማንንም የማይንቅ በመሆኑ ለታማኞቹና ለወዳጆቹ ለነቢያትና ለሃዋርያት የገለጸውን ሚስጥረ መለኮት እንዲገልጽላቸው ፈቃዱ ሆነ ። በተለመደው በረመዳን ጾም ወር ውስጥ እንድ ስፋቱ ሜትር ተኩል በሜትር ተኩል የሚሆን የካብ ጎጆ እስሩና ከሰው ተለይተው ለሰባት ቀኖች ሱባኤ ገብተው ለታላቁ እምላክ በጾምና በጸሎት በንጹህ ህሊና ተማእጽኖአቸውን እቀረቡለት ።

ሲጸልዩ የሚደጋግሟቸው ቃላት የሚከተሉት ነበሩ። “ ምስጋና ለዚያ ጌታ ነው በሰማያት ባለው ዙፋን ለተቀመጠው ታላቅነቱን ለገለጠ ክብሩንም ፍቅሩንም ምስጋናውንም በመላእክት ፊት ለገለጠ አንድም የሚወዳደረው ጓደኛ የለውም ግዛትም ሁሉ የሱ ነው ህያው የማይሞት እለማትን በሙሉ ሁሉን የሚችል አሜን ። “ እያሉ ይጸልዩ ነበር ።

የሱባኤ ጸሎት እንዲያደርጉ የተገደዱበት ምክንያት ከንጉሡ ነገሥቱ ባለሟሎች ከነብላታ ኪዳነ ማርያም ጋር ባደረጉት ግጭት በጥብቅ ይፈለጉ ስለነበር የሚደርስባቸውን ሁሉ በትህትና በታማኝነት እንዲያስችላቸው ነበር ። ይህን መሳይ ጸሎት ዳንኤል ምህረት ከሰማይ እምላክ ለማግኘት የጸለየው በዳንኤል ምእራፍ 2 ቁጥር 20-24 እንዲህ ይላል ።

...ጥበብም ሀይልም የእርሱ ስለሆነ
እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ፡፡
እርሱ ጊዜአትንና ወራትን ያፈራርቃል ፤
ነገሥታትን ወደ ዙፋን ያመጣል ፤
ከዙፋንም ያወርዳል፣ ጥበብን ለጠቢባን
ዕውቀትንም ለአስተዋዮች የሚሰጥ እርሱ ነው፡፡
እርሱ ጥልቅ የሆነውን ምስጢርና የተሰወረውን
ነገር ይገልጣል፤በእርሱ ዘንድ ሁልጊዜ ብርሃን
ሰላለ፥ በጨለማ የተሰወረውን ያውቃል ፡፡
የቀድሞ አባቶቼ አምላክ የሆንህ ጌታ ሆይ!
አመሰግንሃለሁ፣ ከፍ ከፍም አደርግሃለሁ፤አንተ
ጥበብንና ኀይልን ሰጥተኸኛልና፣ ጸሎታችንንም
ሰምተህ የንጉሡን ሕልም ገልጠህልናል ፡፡ ...

የሸህ ዘከርያሰም ራእይ የጳውሎስን ራእይ ይመስላል ጳውሎስ ክርስትያኖችን ለማሳድድ ሲገሰግስ እራሱ ክርሰትያን እንዲሆን ጥሪ በራእይ መጣለት የሐዋርያ ስራ ምእራፍ 9 ቁጥር 3-6

.. ሲሄድም ወደ ደማስቆም በቀረበ ጊዜ በእርሱ ዙሪያ በድንገት ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ ፡፡ በዚየን ጊዜ በምድር ላይም ወደቀ፤ "ሳኦል ሳኦል ለምን ታሳድደኛለህ?" የሚል ድምጽም ሰማ ፡፡ ሳኦልም "ጌታ ሆይ፤ አንተ ማነህ?" አለ፤ እርሱም " እኔ እንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ፤" "አሁን ግን ተነሳና ወደ ከተማ ግባ፤ ልታደርገው የሚገባህም ከዚያ ይነግርሃል አለው " ፡፡

ሸህ ዘካረያስ በሱባኤ ጸሎት ውስጥ እንዳሉ ያሉበት ቤት በልዩ ስሜት ተሞላ እይናቸው የሚመለከተው



እንግዳ ነገር ሆነባቸው በራእይ አንድ ሰው ሲያዩ የሚመጣው ከምስራቅ ነበረ ፡፡ ቁመቱ እረጅም የሆነ ነው ይላሉ መልኩም የተዋበ ጸጉሩም የተሰራ ነው መልኩም የተዋበ ከመሆኑ የተነሳ በስው ግምት አይመጠንም ወደኔ ቀረበና በቃሉ ዘካርያስ ብሎ ጠራኝ የእግዚያብሔር ባርያ ወደኔ ቅረብ አለኝ ፡፡ እግዚያብሔር በቃሉ ላከኝ የቃሉን ትርጉም ግምቱን እንድታውቅ ሲለኝ እኔም እሽ እልኩት ከራሴ ላይ እፍ ቢልብኝ እስከ እግር ጫማየ ድረስ ተሰማኝ ከዚህ በፊት ቁርአኑን የማነበው ያለማስተዋል ነበረ የዚያን ጊዜ ትርጉሙ ግልጥ ብሎ ታየኝ ፡፡ ብለዋል ፡፡

ሁለተኛ ጊዜ የታያቸው ራእይ ከዚያው የጸሎት ስፍራቸው እንዳሉ እርብ ሌሊት በዶሮ ጩኸት ሶስት ታላላቅ ሰወች የተከበሩ እሁንም በሰው እገላለጽ ለማስረዳት ክብር ያላቸው እንደ ደናግል ያሉ መልካቸው አንድ የሆነ መጥተው ከመካከላቸው አስቀመጡኝና ልጃችን ዘካርያስ አትዘን ደስ ይበልህ የትርጉሙን ነገር ልንገልጽልህ መጥተናል ፡፡ ልንፈጽምልህ ነውና የበረታህ ሁን ቁርአኑንም በትክክል ተርጉመው ነገር ግን እኛም አንለይህም ከአሪትና ከወንጌል የማይገጥሙትን የቁርአን ቃል አይተህ አስተካክለው እረመው ፡፡ ብለው ከተናገሩ በኋላ ሶስቱም ሰወች ወደሰማይ አንድ ሰው ሆነው ሶስትነታቸው ወደ አንድነት ከፊቴ ላይ ተለውጠ ሄደ ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደመናና ዝናብ መጣ እመጣጡም ሀሐይ መውጫ ነበር ፡፡ የሚሄደውም ወደ ሀሐይ መግቢያ ነበር በዚች ዓለም ላይ ነው እኔም እሻቅቤ ስመለከት ነበር አንድ እካል መልሶ ከኔ ጋራ ሆኖ እጄን ይዞ አይዞህ አንለይህም አለኝ ፡፡ የበረታህ ሁን አለኝ ፡፡ ይህን ራእይ ያየሁት በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በነገሡ በሶስተኛው አመት ነው ይሉ ነበር ፡፡

ይህም ከእግዚአብሔር ለመሆኑ የታወቀ ነው ። ለሚመለከተው ለሚያስተውለውም የበቃ ራእይ ነው ብለዋል ።

ሸህ ዘካርያስ አሁን ብቻቸውን ይሆኑና ሲያስቡ የቁርአን ትርጉም ከብሉይ ከሀዲስ ብዙ ልዩነት እንደሌለው ተገነዘቡ ። አባቻውም ከነ አፄ ቴወድሮስና ከነአፄ ዮሐንስ ብሸሽ ለማምለጥ ችየ ነበር ። ከላይኛው ንጉሥ ለምን አመልጣለሁ ድሮም የያዝኩት ሃይማኖት እውነት ነው በማለት ነበር እንጅ አንተ የፈጠርከኝ አምላክ ካልተደሰትህበት ይቅርበትና ፈቃድህን እታዘዛለሁ ብለው ሀሳባቸውን ቆረጡ ።

ለተጠሩበትም ሲዘጋጁ ስራቸውን ከመጀመራቸው በፊት መላ ኢትዮጵያን እየተዘዋወሩ እንዲጎበኙ ታዘዙ ። ይህም የሚገለጽላቸው ባደረባቸው መንፈስ አማካኝነት መሆኑን ደጋግመው ተናግረዋል ። የፈቀደውን ሚስጥር ሲነግራቸው በወደደ ጊዜ ብቻ ይነግራቸዋል እንጅ እባቸው ንገረኝ ብለው ለመጠየቅ ካለመቻላቸውም በላይ በፈቃዱ በሚነግራቸውም ጊዜ እጅግ ከባድ ድክመትን የሚያደርስባቸው መሆኑን ሲገልጡ ስወች ስለተለያየ ጉዳይ አምላክ ምን አለ ብለው ሲጠይቋቸው ጠንቋዩ አደረገኝ ይሉ ነበር ይባላል ።



## ምእራፍ 5

## የሸህ ዘካርያስ ጉዞ

ከተከዜ ወንዝ ማዶና ማዶ ከሚገኘው ወይና ደጋና ቆላ አገር አለፍ ብለው አገር አይተው የማያውቁት ሸህ ዘካርያስ ያደረባቸው መንፈስ የተጠሩበትን ስራ ከመጀመራቸው በፊት መላ ኢትዮጵያን ሊያስጎበኛቸው በፈለገው መሠረት ከቤታቸው ወጥተው ጉዞ ጀመሩ ። ታናሽ ወንድማቸው አቶ ዋሴ ጀብሪል መድረሻቸውን ለማየት ይከተሏቸው ነበር ። ሸህ ዘካርያስም የተከዜን ወንዝ ተሻግረው የነገላን አቀበት ሲጨርሱ ወለል ባለው ሜዳ በጋይንት አቋርጠው ወደ ናታቸው አገር ወደ ምክሬ ደረሱ ። የናታቸው ወንድሞች ሲመለከቷቸው የሚጠይቁትና በሚሰጡት መልስ ልዩ ፍጥረት ሆኑባቸው ። ሸህ ዘካርያስ በክርስቲያን ወገኖቻቸው በጣም የተጠሉ ነበሩ ምክንያቱም የናቱን ትቶ ያባቱን የያዘው እያሉ ይንቋቸው ነበር ። እንዲያውም የእህታችን ልጅ ማለታቸው ይቅርና ዘመድ ነው ማለት እንኳ አይወዱም ነበር ። ምክንያቱም በአፄ ቴወድሮስና በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት እስላሙ ሁሉ እየተገደደ ሲጠመቅ እህታችንና ልጆቿም ይጠመቁልናል ብለው ተስፋ ሲያደርጉ እንዲውም የነገላን እስላም ሁሉ አሳድመው የሰሩትን ያውቃሉና የነገላ ሰው አባ በግዲ እንደሚላቸውም ያውቁ ነበር ። ስለዚህ ምክሬ ከተባለው ከናታቸው አገር በደረሱ ጊዜ ዘመዶቻቸው ቢጠሏቸውም ሸህ ዘካርያስም የሚያስወድድ በሰው እንደበት ሊገለጽ የማይችል ራእዩን ካዮ ወዲህ ስላደረባቸው መናገር ሲጀምሩ ሰውን ሁሉ አዎን አዎን የሚያሰኝ ለማዳመጥ የሚናፈቅ አንደበት እንኳን ለዘመድ ለባዳ የሚያኮራ ስውነት ስላደረባቸው ጠይሙ ፊታቸው ለሚመለከታቸው ገጸ ግርማ ሞገስ ስለከበባቸው የኛ ነው ማለቱን ለመጥላት በጣም ተቸገሩበት እንዲያውም የሚከተላቸው ታናሽ ወንድማቸው ከቅላታቸውና ከመልካቸው ቅናት

ከቁመታቸው ዘለግታ የተነሳ የሚመለከታቸው ሁሉ አየ ሰው ይህን እህል እያሉ በልዩ አማርኛ ይህ ይውደቅ ለማይባል ሰባዊነታቸው እየተገረመ ያልፍ ነበር ። ዘመዶቻቸውም ወይ በፍታ ወሸባ ወሸባውን ወልዳ ነበር እስላም ሆኑና ምን ይሆናል እያሉ ሲወያዩ ጎረቤቶቻቸው ደግሞ ታላቅየውማ ከመልኩም ግርማ ሞገሱ እና ያንደበቱ ውበት ምን ወንዝ አፈራው እያሉ በመደነቅ ሲያስተናግዷቸው ከዋሉና ካደሩ በኋላ ወደ ጎጃም እንደሚሻገሩ ስለገለጡላቸው ሰላም ይመልሳችሁ ብለው ሸኟቸው።

ከምክሬ የተነሱ እስቴ መካነ ኢየሱስ የነደጃዝማች እሸቱ ሃይሌን ከተማ አቋርጠው ወደ እንዳቤት ወደነ አባምድር ካሳ አገር ደረሱ ። አባምድር ካሳም የተለመደ እንግዳ አቀባበላቸውን ሲፈጽሙ እንደ አብርሃም የእግዚያብሔርንና የመልአክት እንግድነት እንዳሳደረው ልዩ ግርማ ሞገስ የሰፈረበት በእግዚአብሔር መንፈስ ጸጋ የተጎናጸፈ ሰው ስለመጣባቸው ከተዋበው አዳራሽ ከሚገኝ የእንግዳ መቀበያ አልጋ ልዩ ባህርጃን የመሰለ ጀንዴ ተዘርግቶ ከዚያ እንደተቀመጡ ተጋብዘው እግራቸውን ካጠቧቸው በኋላ ጠላ ቢያቀርቡላቸው አለመጠጣታቸውን ስለገለጡላቸው ወዲያው ማር ተበርዞ በቅቤና በአዋዜ የታሸ እርጎ የነጭ ማር ሰፈፍ በመሰለ ጤፍ እንጀራ ተፈትፍቶ ስለቀረበላቸው ለእግዚአብሔር መዳኘት ምን ያህል የሰውን ጠባይ እንደሚያሳምረው ባደረባቸው መንፈስ አማካኝነት ሲመለከቱ ለሰማይ አምላክ ምስጋና ሲያቀርቡ በምኞት አድረው ሲነጋ በሚገባ ተጋብዘው ያባይን ቁልቁለት ተያያዙት ። አባይን ወንዝ ባዬ ፋሲል ድልድይ ሲሻገሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት ከአራት መቶ አመት ገደማ አስቀድሞ የሰሩት ድልድይ መሆኑን ሲመለከቱ አምላክ ታላላቆቹን ሰወች ለታላላቅ ስራ የሚጠራ መሆኑን ስለተገነዘቡ እሳቸውም በተጠሩበት ሥራ ድርሻቸውን ለሃገራቸው ማበርከት እንዳለባቸው በሰፊው ተረድተዋል ።

ባባይ ሸለቆ ሞጣን አድርገው ወደ ደጋዳሞት በማለፍ አባይን አሸንጥቃ ታጥቃ በመልካም ሰብል የኢትዮጵያን ሕዝብ የምታጠግበውን ጎጃምን ደህና አድርገው እየተመለከቱ በደብረማርቆስ አቋርጠው እንደገና አባይን በመሻገር ወደወለጋ ክፍለህገር ወደ ለቀምት ከተማ አለፉ ። በወለጋ ወርቅ የሚለቀምበትን የኢትዮጵያ ደጋ፤ ወይናደጋና ቆላ መሬት በመመልከት አልፈው ካባጅፋር አገር ጅማ ደረሱ ። ጅማን ሲመለከቱ ሰርከአበባ የሆነችውን ለምለሟን የኢትዮጵያን አካል እየገረማቸው ሲጓዙ በየደረሱበት የሚያገኟቸው የእስልምና እምነት የተቀበለው ሕዝብ ከልክ ያለፈ አክብሮት እያሳዩ ከኛ ጋር የእስልምናን ወግና ሕግ እያስተማሩ ይቀመጡ በማለት የማያውቃቸው ሕዝብ ይለምናቸው ነበር ። ከሌያቸውን ዘርጋ አድርገው ከዛያ ላይ ተቀምጠው እንደ መረዋ የሚንቆረቆረው ድምጻቸው ለስግደት ጸሎት ሲስማሩ ያዩዋቸው ሁሉ ከሳቸው ለመለየት አይወድም ነበር ። በዚህ አኳኋን ከጅማ አልፈው ወደጉራጌ አገር ሲደርሱ አሁንም እኒህን ግርማ ሞገስ የከበባቸው ሽህ ዘካርያስን ሲመለከቷቸው እስላሞቹ እራሱን ሙሐመድን ያዩት ያህል መስሎ ስለሚስማቸው ለሰው ሊሰጠው የሚገባ ክብር ሳይጎድልባቸው ጉራጌን አገር አቋረጠው ወደ አዲስ አበባ ደረሱ ። አዲስ አበባም በደረሱ ጊዜ እራሳቸውም አንድ ቀን እንደሚያብቡባት በመንፈስ እየተመለከቱ አዲስ የተቆረቆረችውን አዲስ አበባን ለጥቂት ጊዜ እየተዘዋወሩ ከጎበኙ በኋላ ጉዟቸውን በደብረ ብርሃን አድርገው ወደወሎ ቀጠሉ ።

የወሎ እስላሞች ሲመለከቷቸው የወዴት አገር ታላቅ ወለይ መጣልን እያሉ በደንብ እየተቀበሉ ከማስተናገድ በቀር ከዚህ አብረውን ይቀመጡ እያሉ ይለምኗቸው ነበር ። እሳቸውም ገና የምንፈጽመው ብዙ እንቅስቃሴ ስላለ እላህ ከዚህ እንድንቀመጥ አልፈቀደም ብለው ሲናገሩ ከግርማ ሞገሳቸው የተነሳ መልስ ለመስጠት ህዝቡ ስለሚፈራ ጸጥ ይል ነበር ። ከወሎ ተነስተው በሸድሆ አቋረጠው መቄትን አድርገው ከቤታቸው ላስታ አውራጃ አይና ብግና ከተባለው ቀበሌ ጣርና ደረሱ ። በስላም በመመለሳቸውም ከአመት በላይ የተለዩዋቸው የወንድማማቹ ቤተሰቦች በጣም ደስ አላቸው ።



## ምዕራፍ 6

## ሸህ ዘካርያስ የተጠሩበትን ሥራ መጀመር

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት መጀመርያ ላይ በገባው ክፉ ቀን በመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከባድ ሸክም ወደቀበት ። ያንየ ሸህ ሙሐመድ አማኜ ከደብረታቦር ተሰደው ወደቋሊሳ መውረዳቸውን በምዕራፍ 3 ገጽ 12 ላይ እንደገለጥሁ የሚታወስ ነው ። ቋሊሳ እንደተቀመጡ ካባቴ ሌላ ምክትሎቻቸውን ሁለት ወንድ ልጆች እንደ ወለዱ ክፉው ቀን ገባ ሀብታም የነበረው ባንድ ጊዜ እንዴት ድህነት እንደ ገባ ለማስረጃ ያህል በዚያው አካባቢ ከብታቸው ሸህ የሚሞላ ሁለት ጊዜ በጨጓራ የታጠቡ ይህም ሁለት ሸህ ከብት ነበራቸው ማለት ነው ። ስማቸውም ገብሩ አባየ የተባሉ ከበርቴ ነበሩ ይባላል ። ያ ሁሉ ከብት በአንድ ሳምንት ስላለቀ እንዲህ ተባለ

" የስማም ጉድ አለ ያየም ተደነቀ፥
የገብሩ አባየ ከብት በሳምንት አለቀ ።"

በዚህ ዓይነት ለገባው ችግር ተከዜ ማዶ ያለው የላስታና የዋግ አውራጃ ለስደት እመች ስለሆነ የጎንደር ክፍለሀገር ህዝብም ወደ ዋግ ተሻገረ ። በዚያህ ጊዜ አያቴ ሙሐመድ አማኜ ባለቤታቸውንና ሶስት ልጆቻቸውን ይዘው በስቆጣ አውራጃ ድህና ወደተባለው አካባቢ ተሻገሩና ላማ ከተባለው መንደር ባለቤታቸውናና ሶስት ልጆቻቸውን ትተው በቅሎቻቸውን ጭነው እህል ፍለጋ በሄዱበት ጊዜ አንዱን ህጻን ኩፍኝ ገደለባቸውና እናቲቱ አንድ እሬሳ ሌላ ሁለት እርሀብ የሚቆላቸው ልጆች ይዘው ሲያለቅሱ እርሀብ ያጠቃቸው ዘመዶቻቸው የሞተውን ህጻን ሲቀብሩላቸው በእንግድነት ትንሽ የጭራሮ ደጃፍ ያላት ጎጆ ዘመድ ስለሰጣቸው ከዚያ ተጠግተው ተቀምጠው ነበር ። ምግብ እናገኛለን እያለ የሚሰደደው

ሕዝብ በየመንገዱ ስለሚሞት ቀባሪ በማጣቱ ጅብ ይበላው ስለነበር የሰው ስጋ መብላት የለመደ ጅብ ከቤት ውስጥ እየገባ ሰው መውሰድ ጀመረ ፡፡ ወይዘሮ ለምለም አባቴንና ምክትል ወንድሙን ይዘው ከተጋደሙበት ጎጆ ደጃፉን ጥሶ ጅብ ወደቤት ይገባና ያባቴን ታናሽ ወንድም ከተኛበት አንስቶ እወጣለሁ ሲል የልጁን ሁለት እግር እናቲቱ ይዘው እየተጓተቱ ወደ ደጅ ሲወጡ እሪ እያሉ ሲጮሁ በመንደር የነበረች አንዲት ውሻ ወይዘሮ ለምለምና ጅብ በሚጎትቱበት ወቅት መጥታ ጅቡን በመንከስ ፈንታ የሴትዮዋን እግር ነከሰቻቸው እርሀብ የወጋው ሕዝብ ምንም ሊረዳቸው ባለመቻሉ ብዙ ጊዜ ከተጓተቱ በኋላ ነጥቋቸው ይዞ ሲሄድ እማማ ወሰደኝ እያለ ሲጮህ እሚያሰጥለው ጠፍቶ ይዞት ሄደና በላው ፡፡ በዚህ ዓይነት ክፉው ቀን ሕዝቡን በሚያሰቅቅበት ጊዜ ልጅ አሳድጋለሁ ብለው እህል ፍለጋ የሄዱት ሸህ ሙሐመድ አማኔ እህል ጭነው ቢመጡ አንዱን ልጃቸውን ኩፉኝ ገሎት ሁለተኛውን ልጅ ጅብ በልቶት ስለደረሱ የከበደ ሀዘን ደረሰባቸው ፡፡ ( ይህንን አያቴ ወይዘሮ ለምለም እራሳቸው ናቸው ያጫወቱኝ)" ፡፡

እንዲሁም ብዙ ዘመዶቻቸውና ጎረቤቶቻቸው ወደ ድህና ተሰደው ከዝች ላማ ክተባለች መንደርና ባካባቢዋ የሰፈሩ እስላሞች ከክፉው ቀን በኋላ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ፡፡

1ኛ) አቶ ካሳሁን ማሩ
2ኛ) አቶ ደስታ ማሩ
3ኛ) አቶ መንገሻ ደረሰ
4ኛ) አቶ ይሄ አብድራህማን
5ኛ) ሸህ ሙሐመደ አማኔ
6ኛ) አቶ ወርቅነህ አደም



7ኛ) አቶ አብድራህማን መሐመድ
8ኛ) አቶ ገላው እሸቴ
9ኛ) አቶ ትኩነህ ሰዋዲቅ
10ኛ) አቶ ሐሽሜ ሙሐመድ
11ኛ) አቶ አልቃድር
12ኛ) አቶ ወንድማገኘሁ አሳረህመት
13ኛ) አቶ ፈንታ ደሰታ
14ኛ) አቶ ዓሊ የአገስ
15ኛ) አቶ እሸቴ
16ኛ) አቶ እስማኤል ዓሊ
17ኛ) አቶ የኑስ ይብራሂም
18ኛ) አቶ ሐሲም
19ኛ) አቶ አህመድ ውሴን
20ኛ) አቶ ውሴን
21ኛ) አቶ ወንድማአገኘሁ
22ኛ) አቶ ዋሲሁን
23ኛ) አቶ ሐሰን ሰዋዲቅ
24ኛ) አቶ ሐሮን ሰዋዲቅ
25ኛ) አቶ ፈንታየ ሰዋዲቅ
26ኛ) አቶ የኑስ
27ኛ) አቶ አደም
28ኛ) አቶ ይብራሂም
29ኛ) አቶ በድሩ ምሳ

ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘሩት አዛውንቶችና ስማቸውን የማላውቃቸው ብዙ ሰዎች ላማ ሰፍረው ክፉውን ቀን ላስወገደላቸው አምላክ ምስጋና ሲሰጡ ሌላ ደግሞ አምላክን የሚያመሰግኑበት እግዚአብሔር መልእክተኛውን ላከላቸው ፡፡ ሸህ ዘካርያስ የጎንደርን፥ የጎጃምን ፥ የወለጋን ፥ የጅማን ፥ የጉራጌን ፥ የሸዋንና የወሎን ሕዝብ ጎብኝተው ከተመለሱ በኋላ ልዋል ልደር ሳይሉ ወዲያው ተነስተው ከቤታቸው በላይ ያለውን

የቆቦን ተራራ ዘልቀው ወደ መረብ ወንዝ ሲመለከቱ በድህና ወረዳ ከሲልደ ተራራ ግርጌ የጎልጎታን ሸንተረር ወርዶ አንገት በታች ላማ የተባለችውን ጎጥ ከቦ ድርድር ያለውን መንደር ተመለከቱና ስራዮን የምጀምርበቱ መንደር ይህ ነው አሉ ይባላል ::

ሸህ ዘካርያስ ወደዛች መንደር በደረሱ ጊዜ የላማና የአካባቢው ሰወች ለንግድ ወደ መቀሌ ለመሄድ ተነስተው ደረሱ :: በብዙ መቶ የሚቆጠር በቅሎ የጫነ ነጋድራሱ ወደቤቱ ጋብዞ ስላስገባቸው በመንደሩ ያለውን ነጋዴ ሁሉ ሰብስብልኝ አሉና ለነጋድራሱ ተናገሩ :: ነጋድራሱም በቶሎ ጀማውን አስጠርተው ፈቃዳቸውን ሲፈጽሙ እምላክ የዛሬውን መንገድ አልፈቀደላችሁምና እንዳትሄዱ ሲሉ ተናገሩ :: ቆለኛ ነጋዴ ሸሁ ብንሄድ ምን እንሆናለን ? ብለው አዙረው ጠየቋቸው ጠንቋዩ አደረገኝ አሉና እኔ አምላክ ተናገር ያለኝን ብናገር አነሰኝና ቢሄዱስ ምን ይሆንባቸዋል ብየ ለመጠየቅ አቅም አለኝን ? :: ነጋዶቹም ወረታችን ሁሉ ገዝተን ለመሄድ ስንነሳ አትሂዱ ቢሉን ማን ይሰማል ብለው ጉዞዋቸውን ጀመሩ :: ተጉዘውም መቀሌ ከተማ በደረሱ ጊዜ የጣሊያን የጦር ሠራዊት ከአድዋ ወደ አላዤ ተራራ እየገሰገሰ መቀሌ በደረሰ ጊዜ የጦር መሳሪያና ስንቅ የሚያጉዘው ከብት በርሀብና በመንገድ ብዛት በመድፍና በከባድ መሳርያ ጭነት ከመድከሙም በላይ ያልታሰበ የከብት ህመም ገብቶ የወታደሩን ከብት ጨርሶበት ሳል እነዚህ ነጋዴዎች ስለደረሱ መቀሌ በገቡ በማግስቱ የጣልያን ወታደር መጣና ከሜዳው ላይ የሚለቅመውን በቅሎና ፈረስ አህያም ሳይቀር ነድቶ ሄደ ምነው ብለው ለጦር መሪው ጩኸት ቢሄዱ የሞተበትን ከብት ሬሳ ተሸከሙ እያለ ከሰፈር ወደ ሜዳ እንዲጥሉ የጠነባ የፈረስና የበቅሎ የግመልና የአህያ ጥንብ



ሲያስጎትታቸው ዋለ :: በማግስቱ መጥቶ ከሰፈሩበት የከብቶቹን መጫኛና ዳውላ ድልዳል አምጡ ብሎ ስላዘዘ ዳውላና መጫኛ እንስጥም ያላችሁ እንደሁ ወረታችሁ ሁሉ እንዲዘረፍ ይሆናል በሚል ድምጽ ባሰሙ ጊዜ ወዲያው ዳውላና መጫኛውን አስረከበው አንዳንድ ደካማ አህያ ለጭነት የማያገለግሉትን ትቶ ስለሄደ ወረታቸውን ከስረው እየሸጡ ያሁሉ ነጋዴ ባዶ እጁን ተመልሶ መጥቶ ሸሁ ይቅርታ ያድርጉልን ቃለዎን አንሰማም ብለን ከእንደዚህ ያለ መከራ ወደቅን ሲሉ እየተናዘዙ ከዚህ ቀን ሌላ ከቃላቸው ዝንፍ ላለማለት ተሳሉ :: ሸህ ዘካርያስም ቃሉ የኔ አይደለም ከመንፈስ የተላከ ነበር አንሰማም በማለታችሁ የዘራችሁትን አዝምራችኋል ለወደፊቱም ቢሆን ከራሴ አልናገርም የተላከሁትን እንጅ ስለዚህ መልእክቱን ስትታዘዙ የፈጠራችሁን ታዘዛችሁ እንጅ እኔን የታዘዛችሁ እንዳይመስላችሁ :: ሲሉ መከሯቸው::

ሸህ ዘካርያስ በዋግ ሹም ግዛት አመድ ወርቅ አውራጃ ድህና ቀበሌ ላማ ከተባለችው ጎጥ ስራቸውን በጀመሩ ጊዜ የሚያስተምሩበት በቂ መሳርያ ለማግኘት ችግር ስለነበረ ነጋዴዎቹ ወደ መቀሌና አስመራ ከዛም ወደ ምጽዋ ለንግድ ሲሄዱ ከሶስትና ካራት ያልበለጡ ቁርአን ነበሩዋቸው :: ስለዚህ ወጣት ወጣቱን ጠርተው የዋንዛውን እንጨት አንድ ክንድ እርዝመት ግማሽ ክንድ ስፋት እያስጠረቡ ለስለስ አድርገው ሲያቀርቡላቸው ይህን መሳዩን ጥርብ እንጨት ሉህ ብለው ይጠሩታል :: ከዚያ ላይ የአረብኛውን ፊደል አዥጎርጉረው ጽፈው ሀምሳ ስልሳ የሚሆኑትን ተማሪወች በየእጃቸው ፊደል ሰጧቸው ወዲያው ፊደል በጨረሰው የንባብ መልመጃ እራሳቸው እየጻፉ ስለሚሰጧቸው እንዲሁም ተማሪዎች ከየመጡበት ቁርአን ስለሚያመጡ በጥንቃቄ የተያዘው መጽሐፍ

ስጊዜው በቂ ስለሆነ በመቶ የሚቆጠሩት ተማሮቻቸው ሁሉም ወዲያው ቁርአኑን ያነቡ ጀመር ።

የሸህ ዘካርያስ የማስተማራቸው ዝና እንኳን በኢትዮጵያ ባህር ተሻገረ ። ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሚሰጠው ትምህርት ባንድ ጊዜ ማሰረጃ ስለሚሰጥ ከሳቸው የተማረው ደረስ ሁሉ ተረድቶ ማስረዳት የሚችልበት ሰጦታ ያገኝ ጀመረ ። ዝናቸውን የሰማው ከሩቅ አገር እየመጣ ትምህርቱን ለመማር የተሰበሰበው ብዙ ሲሆን ጥቂቶቹን ሰማቸው የታወቀውን ከዚህ በታች እዘረዝራለሁ ።

| | |
|---|---|
| 1ኛ) አቶ አህመዲን | ከአድዋ |
| 2ኛ) አቶ አስን አድዋ | ከአድዋ |
| 3ኛ) አቶ ጠቋሬ | ከወልቃይት |
| 4ኛ) አቶ ወንድሜነህ ጠቋሬ | ከወልቃይት |
| 5ኛ) አቶ ገብረእግዚአብሔር | ከጎንደር |
| 6ኛ) አቶ ጌታሁን | ከጎንደር |
| 7ኛ) አቶ መሐመድ አማኔ | ከፋርጣ |
| 8ኛ) አቶ ዋሴ ለምለም | ከበለሳ |
| 9ኛ) አቶ ይሳያስ ወንድምአገኘሁ | ከብናት |
| 10ኛ) አቶ ካሳሁን ወርቅነህ | ከብናት |
| 11ኛ) አባ ሃጅ ገ.እግዚአብሔር | ከሸድሆ |
| 12ኛ) አቶ ገ. እግዚአብሔር ሱዋለህ | ከዋግ |
| 13ኛ) አቶ ሞትባይኖር ጎሹ | ከብናት |

እነዚህና ብዙ የማስተዋል ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የቁርአኑን ፍች ሲከታተሉ ብዙ ተማሪዎች እሳቸው በተማሪነታቸው እስተማሪያቸውን ሸህ ውመርን የጠየቁትን መልስው ጠየቋቸው ጥያቂያቸውም ተውራትና ኤንጂል አሪትና ወንጌል



ከሰማይ አምላክ የተፈቀዱ ለመሆናቸው ቁርአን ይመሰክራል ታዲያ እኛስ እነዚህ መጽሐፍት ብሉይና ሀዲስ እንደሚያዙት ልንኖር አይገባም ? እያሉ ሲጠይቋቸው አንተን ኤልም ተፍሳሪ አድርጎ ማን ሾመህ የተባሉትን ሰው አሁን ኢልም እንደተፈሰሩ ሚስጥር እንዲተረጉሙ ከላይኛው ጌታ ስለተሾሙ በርግጥ ልንታዘዛቸው ይገባል ብለው ገለጡላቸው ። ጥያቄውን በማከታተል እንግዲያ ከክርስትያን ምን ልዩነት ይኖረናል ቢልዋቸው ሲመልሱ ልዩነትማ ሁሉስ ምን ልዩነት ነበረው ከአንዱ ሰው አዳም የተፈጠረው ሁሉ ዳሩ ግን ኃጥያታችን ያመጣብን ልዩልዩ ቋንቋ እንዱን ጉዳይ አንዱ አቁማዳ ሌላው ለቆታ እንዲሁም ቀልቀሎ እየተባባለ ሲታመስ ሲተራመስ ይኖራል እንጅ ብለው ከመለሱ በኋላ በሉ ለሁሉም ጊዜ አለው አሏቸው ።

ሸህ ዘካርያስ በሚጠየቁት ጥያቄ የሚሰጡት መልስ አንድነትን የሚያስገኝ ፍቅርን የሚወልድ ጠብን የሚያሰወግድ የሚያስተሳስብና የሚያደጋግፍ ነገሥታቱ ከሕዝቡ ጋራ ሲጋጩበት የነበረውን መለያየትና የነጻነት ጠንቅ የሆነውን ልዩነት አስወግዶ በአንድነት የሚያስተባብርና የሀገር ፍቅር የሚያሳድር መሆኑን የተመለከቱ ሴቶች እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው ።

የወንዶችን ችግር ሲያቃሉላቸው ስላየን የኛንም ችግር ቢያቃልሉልን ብለን መጥተናል አሏቸው ። የተቸገራችሁበትን መፍትሄውን አምላክ ይሰጣችኋል አትቸገሩ ግለጡልኝ ብለው ሲጠይቋቸው እኛ የተቸገርነው አንድ ወንድ እስከ አራት ሚስት ያግባ ተብሎ ይፈቀድለታል እኛ ግን ለአንዲቱ ሴት አራት ወንድ መፈቀዱ ይቅርና አንድ ለአንድም ማግኘት ሲገባን አንድ ለአራት ብቻ ሆነብን ። ይህ ብቻ

አይደለም እናት እባት የሞተባት ሴት ልጅ ከወላጆቿ ውርስ ስትካፈል ሁለቱ ሴቶች ያንድ ወንድ ፈንታ ብቻ እንዲደርሳቸው እንባላለን ። ይህ ባይበቃ ባል ስናገባ በእኩልነት ለትዳራችን እያሰብነ ቤት ንበረት አቁመን ስንኖር የተቆጣ እንደሆን ውጭ ሲለን ንብረታችን አስረክበን መውጣት ብቻ ነው ። እኛ የሚያስቆጣ ነገር ቢደርስብን ምንም አይታሰብልን ። አኛ ከሌላ ወንድ ብንሄድ አንቄ ልግደል የሚለው ለራሱ ከበላያችን ላይ አጭቶ ይመጣል በይ ንደጅ ይላል ይህ ሁሉ ግፍ ሲፈጸምብን የሚያይ እምላክ ፍርዱ ምን ይሆን እያልን ስንጨነቅ አሁን የእምላክን መልእክተኛ ካገኘነዎት የዚህን ጉዳይ እንዲያብራሩልን እንለምነዎታለን ሲሉ ሴቶች ጥያቂያቸውን አቀረቡ ።

ሸህ ዘካርያስ ለሴቶች ጥያቄ ያቀረቡላቸው መልስ እንዲህ የሚል ነበር ። እምላክ ጥንቱን ሲፈጥር ለአንዱ እዳም እንዲት ሄዋን ፈጠረ እንጅ አራት ሄዋን አልፈጠረም አራት እንዲያገቡ ወንዶች ሲመክሩ ለብቻቸው የመከሩት ነው ። መሐመድም ሶስትና አራት ሚስት አግብተው ቢያዩዋቸው ማስተካከል ለሚፈልግ አንዲት ብቻ ትበቃለች ብለው እንደእምላክ ፈቃድ ምክራቸውን ለግሰዋል ። የኛ ዘመዶች ግን ወንዱ ያፈራውን ለሴቶች እኩል ማካፈልና የሚበቃ ሀብት ያለው ማለቱ ነው ይላሉ ። እምላክ ስለጋብቻ ሀብታምና ድሀ እላለም ለሀብታምም ሆነ ለድሀ እንድ ለአንድ ብቻ ተፈቀደለት እንጅ ። ይህም በአዳምና በሄዋን አፈጣጠር እምላክ ፈቃዱን ስለ ጋብቻ ያለውን ትክክለኛ ፍርድ ለተከተዩ ትውልድ ስላስቀመጠለት እምላክን የሚፈራ እውነተኛ ትውልድ በዚህ መለኮታዊ እቅድ ይመራበታል ።



ካባት ከናት ስለሚወረስ ንብረት እርስትም ሴት ልጅ ከወንድሟ በምንም ማነስ ወይንም መብለጥ የለባትም ። ወንዱም ሆነ ሴቷ ሰው ወደ መሆን መብት የሚመጡ እንደኛ በማያዳላው እምላክ ፈቃድ ሁለተኛ በወላጆቻቸው ፍቅር እንጅ በራሳቸው ፈቃድ ስላልመጡ የፈጠራቸው እምላክ ሆነ የወለዱ ወላጆቻቸው የኩልነት መብታቸው ሀብታቸውን ሊነፈጋቸው እንደማይገባ ተናግሬያለሁ አሉና ንግግራቸውን በማያያዝ ስለ ባልና ሚስት ሀብትም ይሁን የኩልነት መብት የተጠበቀ መሆኑን አስረዷቸው ።

የወይዛዝርቱ ጥያቄ ሲያበቃ በመልሱ ከተደሰቱት እንዱዋ ወይዘሮ አንስታ "አንተም እኩል ትሞት ይሆናል አለች" ሌላይቱ መለስ አድርጋ "እንቅልፉም ሲበዛበት ነው" ስትል ሌላዋ ደጋሞ "ምን ትላለች ደጉን መምህር እረፍት አልቦ ልታኖሪው ነውን ?" ብትላት መለስ አደረገችና "ለጊዜው ቢያንቀሳፋ እንኳ በትንሳኤ ቀን ይነሳል ማለቴ ነው እንጅ" እየተባባሉ ተመለሱና ይህን የመሰለ የኩልነት ጊዜያቸውን በዛው ጊዜ ጀመሩ ።

ተማሪዎቻቸው ደግሞ ሌላ ከባድ ጥያቄ አመጡባቸው የተጠየቁትም የሚከተሉትን ነው የይሳ ነገር በጣም ከብዶናል ለመሆኑ ማነው እሱ ? የሚል ጥያቄ ደረሳቸው ቁርእን እቅርበው አሊፍ ። ላም ። ሚም ። የሚል አውጥተው ካነበቡ በኋላ ፦

አልፍ፤-ማለት መጀመሪያውና መጨረሻው የማይታወቅ የሁሉ አባት የሆነው እምላክ ነው ።

ላም፤- ማለት የእምላክ ቃል ይሁን ባለጊዜ የፈለገው ሊሆንለት የሚችል ከማይታየው ከባዶው ቦታ ይሁን ባለጊዜ ይሁን ያለው

የምንኖርባትን ምድር እንድትሆን ያደረገው ሁን አለ ሆነ የሚለው ቃሉ ማርያም ልጅ ትወልዳለች ብሎ ቢናገር አረገዘች ይህ ሆኖ አያውቅም ሴት ያለወንድ የማትወልደው ላምላክ የሚሳነው የለምና ድንግል ያለወንድ አርግዛ ወንድ ልጅ ወለደች ይህ የአምላክ ቃል እርሱ አምላክ የሆነ ይሳ የሱስ ነው ።

ሚም ፤ ማለት አለምን በፈጠረ ጊዜ በህዋው ላይ ሲሰፍ የነበረውን ሲፈጥር በሰው አፍንጫ ላይ አምላክ እራሱ እፍ ያለበት እስትንፋስ ለሰው ህይወት ለመስጠት ያስቻለ የአምላክ መንፈስ ንፋስ እስትንፋሱ ማለት ነው ።

እሊህ ሶስቱ ሶስት አምላክ አይባሉም ግን አንድ አምላክ ነው ብለው አንድ በሶስት የተሸረበ ገመድ ወስደው ይህን ሶስት ትሉታላችሁ ወይንስ አንድ ብለው ተማሪወቹን ሲጠይቋቸው አንድ ገመድ ነው አሉ እሳቸውም ገመዱን ፈርቅቀው ሶስት ሸርብ አንድ ገመድ መሆኑን እንዳያችሁ የአሊፍ፤ ላም፤ ሚም ፤ ምሳሌ ይህ ነው አሉና አሊፍ ዘሩ አካሉ ፤ ላም ፤ከላሙ ቃሉ ፤ ሚም መንፈሱ እስትንፋሱ ከአንድ ሰው የሚገኙት ጠባዮችም አካል ቃልና እስትንፋስ ሌላ መልካም የሆነ መግለጫ ነው ሲሉ ለተማሪወቻቸው አስረዱዋቸው ።

ተማሪዎቹም ጥበቡ የማይመረመር አምላክ ይህንን የገለጠ ምስጋና ይድረሰው ብለው ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ወደየእለት ተግባራቸው ተሰማሩ ።



ሸህ ዘካርያስም ጸሎት አዘውትረው ሲጸልዩ በቀን ሶስት ጊዜ እንደ እስላሞች ልማድ ወደ መካ መዲና አይዞሩም ነበር እስላሞቹ ምነው ልማዳችን አፈረሱብን ወደ መካ ወደ መሐመድ መቃብር ዞረው መጸለይ አይገባምን ? ብለው ለጠየቋቸው ሲመልሱ እምንጸልየው ለጸሎት ሰሚው አምላክ ስለሆነ ወደ መካ ሳይሆን ወደፈለግነው አቅጣጫ ብንሆንም ሊሰማን ይችላል ። ስለዚህ ጸሎት ልንጸልይ ይገባናል እንጅ ለለአቅጣጫው አይደለም የሚሰማው ብለው በመመለሳቸው እስላሞች ስርአታችንን አፈረሰብን ብለው ተቆጡባቸው ።

ሸህ ዘካርያስ ሲያስተምሩ ይቅርና በአንድ በሁለት ቀን ስብከታቸውን የሚሰማው ሁሉ ልቡ እየተነካ አዎን አዎን አሜን አሜን እያለ ስለሚቀበልና ትምህርቱን የፈጸመውም ዝናቸውን በየመጣበት አቅጣጫ ይዞ ስለተመለሰና ወደ የትወልድ አገሩ በመመለሱ በብዙ ክፍለሀገር ተወዳዳሪ የለላቸው የእስላም መምህር መነሳታቸውን የሚሰማው ወጣት ሁሉ መጥቶ የሚያስተምሩበትን የላማን አካባቢ ስላጥለቀለቀው ይህ ሁኔታ የፈጠረው ችግር በሁለትና በሶስት መቶ የሚቆጠረውን ተማሪ የሚመግቡበት ዘዴ መታጣቱ ነበር ።

## *ምእራፍ 7*

## *ችግሩን ለማቃለል የተገኘ ዘዴ*

ሸህ ዘካርያስ ተማሮቻቸውን ሰብስበው ከእንግዲህ ወዲህ በደህና ተወስነን ለመቀመጥ የማይቻለን ነው ። ዳሩ ግን ስራችን በተስፋፋ መጠን የመኖሪያችንም ጉዳይ በዚሁ ሁኔታ ስለሚስፋፋ አሁን የምስጣችሁን መመሪያ እንድትከተሉ አደራ እላችኋለሁ ። ከዛሬ ጀምሮ እስከለተ ሞቴ ብዙ የምንደርስበት ስፍራ ስላለ ለጉዞ የተዘጋጃችሁ ሁኑ ። በጉዞ የማትተባበሩን በብዙ ልትረዱን ትችላላችሁ እንድነት የሰማይን ሀይል ሰቦ በምድር ላይ ታላቅ ተግባርን ሲያስፈጽም ይታያል ። ስለዚህ እንድነታችሁ ብዙ ስራ መስራት መቻሉን ከተረዳችሁ ወደስፈርም ሆነ ከኔ ጋር በያገሩ እየዞሩ ለሚያስተምሩት ቤተሰቦቻቸውን በተቻላችሁ እንድትረዱልኝ አደራ ። ወደ ስፈር በምንሄድበት ጊዜ ስንቅ ስለሚያሻን በተቻላችሁ ስትረዱን የኛው ተግባር የሚያስገኘውን ውጤት ደስታውንም ሆነ ክብሩን መካፈላችሁ የተረጋገጠ ስለሆነ የእርዳታ ክንዳችሁ እንዲዘረጋልን አደራ እንላችኋለን ።

እላንትም የእስከዛሬ ተማሮች ለወደፊት መምህሮች የሆናችሁ በምንደርስበት ሁሉ ለህዝቡ በረከት ልንሆንለት የምንችልበት ብዙ መንገድ አለ ። ያም መንገድ በየገበያው ወጥታችሁ ብዙ ልዩ ልዩ እቃወችን በቀላሉ በሰው ትከሻ ሊሄድ የሚችሉትን እንደ ወረንጦ፣ መርፌና መርፌ ቁልፍ ልዩልዩ የልብስ ቁልፍ ይዛችሁ ስትጓዙ በባዶ እግሩ በሸህማ ቦታ ተስማርቶ የእለት ተግባሩን ሲያከናውን ብዙ ጉዳት የሚደርስበት ህዝብ ወረንጦ ሲያገኝ ይደስታል ስለዚህ እናንተን ለመቀለብ ደስ ይለዋል ። ምላጭ ሌላ እይነት ሸቀጣ ሸቀጥም ህዝቡ በጣም የሚፈልጋቸውን ከኑሮው ጋር የተያያዙትን ይዛችሁ ተከተሉኝ ብለው ጉዞ ጀመሩ ።



ሸህ ዘካርያስም ከላማ ተነስተው መቂትን፣ ሸድሆን፣ ዋድላና ደላንታን ከጎበኙ በኋላ በላሊበላ አድርገው ሰቆጣ ከተማ ደረሱ ። በተዛዎሩባቸው ስፍራዎች ሁሉ በአረብኛ ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ብሉይና ህዲስ ባማርኛ ሁለቱን እያስተያዩ እንዲሁ ቁርአኑን የተገነዘቡትን እውነት ለሕዝቡ ጌታ ባዘዘው እንደበታቸው በሚሰብኩበት ጊዜ ከሶስት እስከ እምስት መቶ ሰው በተሰባሰበበት ቦታ ሲሰብኩ ቀጠን ብሎ ከሩቅ ለመሰማት የሚችለው ድምጻቸው ካንደበታቸው የሚፈልቀውን መንፈሳዊ በረከት አንድ እንኳ ሳይቀር የተሰበሰበው ሕዝብ ከመነሻ እስከመድረሻው አገልግሎቱን ያስተውለው ነበር ።

በቅዱስ ቁርአን መጽሐፍ የተጻፈውን ንባቡንና ትርጉሙን በማወቅ ማንም ሊወዳደራቸው የማይችል የማስተዋል ችሎታ የነበራቸው ሸህ ዘካርያስ ብዙ ጊዜ ይጠቅሱት የነበረው የቁርአን ቃል በቁርአኑ መጽሐፍ <u>በአንደኛው ክፍል በምእራፍ 2 በቁጥር 87 እና 91-136</u> የሙሴ እሪት የኢየሱስ ወንጌል የነቢያት መጽሐፍ ሁሉ ከላይ ከፈጣሪ የተሰጡ ሲሁኑ የቁርአኑ ቃልም እነዚህ የተዘረዘሩት ስለዚህ ብሉይ ህዲስን የማንቀበልበት ምክንያት የለንም እያሉ ያስተምሩ ነበር ። ሸህ ዘካርያስም በየደረሱበት በሴቶች በኩል ጥያቄ ስርአት 3 ቁርአን ይጠብቁ ይባላል ። አንድ ሁለት ጊዜ ፈትቶ አብሮ መኖር ሲቻል ሶስተኛውን ፍች ግን ሴቷ ሌላ ባል አግብታ ካገባችው ባል ብትፋታ የድሮ ባሏን ለመታረቅ ከፈለገች ልትታረቅ ትችላለች የሚባለው ለምንድነው ? ሶስተኛስ ቢፋቱ ሌላስ ባል አግብታ ካልፈታች የድሮውን ፍች የተፋቱ ባልና ሚስት ሊታረቁ አይችሉም መባሉ ለምንድነው ?

ሸህ ዘካርያስ ይህን ለመሰለው ጥያቄ የሚሰጡት መልስ የሚከተለው ነው ። በእስልምና ጋብቻ ስነስርአት ቁርአኑ በምእራፍ 2 በክፍል 2 በቁጥር ( እንቀጽ ) 230 በሚያዘው መሰረት ነው ። ዳሩ ግን ይህ ስነስርአት ከወንጌሉ ስነስርአት ጋር ፈጽሞ ስለማይስማማ ቁርአን እራሱ ወንጌልም ሆነ ኦሪት ብሉይ ኪዳንም ሆነ አዲስ ኪዳን ከሰማይ ምድር ፈጣሪ የወረዱ ናቸው ብሎ ስለሚመሰክር ቃላቸውን ልንከተል የሚገባው የወንጌሉን በመሆኑ በጳውሎስ መልክት 1ኛ ቆሮንቶስ ምእራፍ 7 1-40 በተለይም ቁጥር 11 ብትፈታውም ሌላ አታግባ ከፈለገች ከእርሱ ጋር ትታረቅ ወንድም ሚስቱን አይተው ብሎ ባዘዘው መሰረት የወንጌሉን ቃል መታዘዝ ይገባናል ። ብለው ስለሚመልሱላቸው ብዙወች የእስልምናን ሃይማኖት የሚከተሉ ሴቶች ወደ ክርስትና ሃይማኖት ለመመለስ በጣም ናፍቆት አደረባቸው አባትና ወንድም አጎቶችም ቢሆንም ተሰባስበው ለሴቶች ነጻነት የእኩልነት መብት እንዲኖራቸው እንዲያስቡበት በየጊዜው ይለምኗቸው ጀመር ሁናቴውም እረፍት የሚነሳ ሆነባቸው ። ስለዚህ ስለአዲሱ የሸህ ዘካርያስ አተረጓጎም ብዙወቹ ሲቀበሉት ሌሎቹ እየተቃወሙ ስቆጣ ከተማ በገቡ ጊዜ የተቃዋሚው ክፍል ሸህ አደም የተባሉትን ነገረፈጅ አድርገው ከሰሿቸው ።



# ምእራፍ 8

## የመጀመርያው ክስ

ሸህ ዘካርያስ ስቆጣ እንደደረሱ በላስታ ውስጥ የዓይነ ቡግና፣ የደንጎባት፣ የገለሶት፣ የላሊበላ፣ የሙጃ፣ የመቄት፣ የሸድሆ፣ የዋድላና ደላንታ፣ እስላሞች በዋግ ውስጥ የድህና፣ የጥላላ፣ የመስቀሉ፣ የጋዝጊቢላ፣ የስቆጣ፣ የጀርባ፣ የኩረም፣ የወፍላ፣ የራያ፣ ዘቦ፣ የጅም፣ እስላሞች እንዲሁም የሰሜን ተራራ የበየደና የደረስጌ እስላሞች የስቆጣን ከተማ ስብስብ አሉባት ። እንደተሰበሰቡም የዘካርያስን አያያዝ ሲመለከቱ በነሱ አንደበት አጥጋቢ ክስ ሊቀርብባቸው የማይቻል መሆኑን የተገነዘቡት ሰዎች ዘካርያስን እንደማንም ብሎ ህይወቱን ማጥፋት እንጅ ከሶ መርታት እንደማይቻል ባደረጉት ጉባኤ አስረዱ ። ሌላው ክፍል ደግሞ አላህ ሀቅ ይወዳል ተላስቶ ቢሆን መላላቱን በህግ ማስረዳትና ፍርድ መቀበል እንጅ ከህግ ውጭ ሠራ ብሎ ህግ አፍራሽ መሆን ሰውን መግደል አይታየንም የሚሉ ነበሩ። በዚህ ሀሳብ በሚተራመሱበት ጊዜ ሸህ ዘካርያስ አምስት ጊዜ ሶላትን ሳይተላለፉ ጸሎት ሲያደርጉ በተለይ የጧትና የማታውን በኩል ቀን የሚደረገውን ጸሎት ከከፍተኛ ቦታ ላይ ሁነው አዛን በማድረግ ድምጻቸውን ሲያሰሙ የላቸው ተከታይ 300-500 የሚሆኑት ሲሰበሰቡ የከተማው ኗሪ እስላሞች ከዚህ ያላነሱ ወደ ጸሎቱ ቦታ ሲመጡ ከሸህ በላይ ለሚሰበሰበው ሕዝብ ስብከት ሲጀምሩ የተቃዋሚው ወገንም ሁኔታውን ለመረዳት ከሕዝቡ ጋራ ቀርበው ይሰሙና ጸሎት ምላሽ ሲሆን ይህ ቃል ከጌታ አልወረደም ማለት አላህን እንደመካድ ያስቆጥርብናል እያሉ ይናገሩ ነበር ይባላል ። በጊዜው ዋግ ሹም ጓልጉል በከተማው ስለነበሩ ሸህ ዘካርያስ ዋግ ሹም ጓንጉልን ተገናኝተው ለጥቂት ጊዜ በከተማቸው እንዲቀመጡ ፈቃድ ስለጠየቋቸው ተፈቅዶላቸው

ተቀምጠው ሳል ዲናችን ( ሕጋችን ) አፈረሰው የሚሉት ወገኖች ሸህ አደም የተባሉትን የእስላሞች መምህር ነገረፈጅ አድርገው ክስ ለማቅረብ ተዘጋጁ ። የቀረበውም ክስ እንደሚከተለው ነበር ።

1ኛ. ሃይማኖታችን ለውጠሀል
2ኛ. ስርአታችንን አፍርሰሀል
3ኛ. ልማዳችንን አስቀተርተሀል
4ኛ. ራእይ አይቻለሁ እያልህ ሕዝቡን ታተራምሳለህ

ስለዚህ እንዳንተ ያለው ከሀዲ ሞት ይገባሀል ሲሉ ክሳቸውን አቀረቡ ። እንደ ጊዜው ዳኝነት ጉዳያቸውን በሚገባ እንዲመለከቱላቸው ከአስር ሸህ ብር በላይ ባጋሰስ ጭነው አምጥተው መተያያ አቅርበው አቤቱታቸውን ከላይ እንደ ተጠቀሰው አቀረቡላቸው ። ዋግ ሹም ጓንጉልም ዳኝነት ማውጣት ፍትህ መስጠት ተግባራችን ስለሆነ ሸህ ዘካርያስም በተከሰሱበት ጉዳይ እሱና ደጋፊወቹ መልሳቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ቀን ተወስኖ ይሰጣቸው ሲሉ አዘዙ ። ትእዛዙም ለሸህ ዘካርያስ ደረሳቸው ።

<u>የመጀመርያ ጉባኤ</u>

በተወሰነው ቀን ይህን ክርክር ለመስማት ከያለበት እስላሙም ሆነ ክርስትያኑ በሰቆጣ ከተማ ሞልቶ ተረፈ ። በቀጠሮው ቀን ዋግ ስዩም ጓንጉል መኳንንቱንና ባገራቸው ውስጥ የሚገኙትን እያሌ ደጃዝማቾች እንዲሁም ታላላቅ ነጋዴወችንና ያደባባይ ሰወች አስጠርተው ለጉባኤ ተቀመጡ ። ከሳሾችም



በጉባኤው ውስጥ ተገኝተው ክሳቸውን አሰሙ ተከሳሹ ሸህ ዘካርያስም ለተከሰሱበት መልስ የሰጡት በቁርአን ምስክርነት ብሉይና፣ ሀዲስ፣ አሪት፣ መዝሙር፣ ነብያትና ወንጌል በእግዚያብሔር የተሰጡ ለመሆናቸው ያረጋግጣል ስለዚህ እኔ የማስተምረው ከነዚህ ቁርአን ከሚመሰክርላቸው መጽሀፍ ውጭ አይደለምና እውነተኛ ሃይማኖት አልለወጥሁም በልብ ወለድ ቃል የሚያስተምርበትን ግን ለስጋቸው የሚመቻቸውን ያልታዘዘውን ለውጬ በታዘዘው መርቻለሁ ።

በእምነትም ሆነ በጋብቻ በውርስ ገንዘብም ሆነ በጠቅላላው እራስን ወዳድ በሆነ አስተያየት የተዘጋጀውን ስነስርአት አምላካዊ በሆነ ስነስርአት ለውጬ አስተምሪያለሁ ።

ልማዳችንን አስቀርተሀል ስምትሉት ክፉ ልማድ ያለእውቀት ይሰራል እንጅ ሰው ከጥንት የቆየ ነው እያለ መልካም ልማድ ሲያገኝ ክፉውን የማይተውበት ምክንያት የለም ። ስለዚህ አንድ ወንድ አራት ሲፈቀድለት አንዲት ሴት ግን የአንድ አሩብ አንድ ለአራት ይድረሳት የሚለውን ልማድና እንዲሁም ስለውርስ ደካማይቱ ልጅ ሴቷ ሲሶ ወንድየው ልጅ ሁለት እጥፍ ይውረስ የሚለውን ልማዳችሁን አፍርሻለሁ ይህ ይፈጸም ብለን ብንፈርድ በወንዶች ላይ ሀሊናችን ስለሚፈርድብን በሀሊና ጅራፍ ስገረፍ ከምኖር አምላክ ያዘዘውን አስተምሬ የመጣብኝን እቀበላለሁ ።

ራእይ አይቻለሁ እያልክ ሕዝቡን ታተራምሳለህ ለምትሉት የራእይ ጉዳይ አምላክ ለጠራው ነው እኔም እንደናንተው የእስልምና ሕግና ስርአት ልማድ የሚያፈርሱትን እንደ አፄ ቴወድሮስ አፄ ዮሐንስ

ያሉትን ባለስልጣን እንኳ ሳልፈራ በልማድ ተገድጀ አሁን እላንት ከምትፈጽሙት የከፋ ስፈጽም ነበር ዳሩ ግን ከእምላክ ዳኝነት ለማምለጥ የሚችል ማንም ባለመኖሩ በእምቢተኝነቴ አባ በግዲ የሚባል ስም ወጥቶልኝ የነበርኩትን በቅን ልቦና የሱባኤ ጸሎት በማደርግበት ጊዜ ሰላሶች በሶስትነታቸው ተገልጠው ዘካርያስ ሆይ ልጃችን ቁርአንን በሚገባ አድርገህ እንድትተረጉም ልንልክህ መጣን ቢሉኝ የታዘዝኩትን በሚገባ ለመፈጸም ደካማ ብሆንም ሁለቱ ወደመጡበት ሲመለሱ እንዱ ከኔ እጠገብ የማይለየኝ ጓደኛየ እናንተ ባታዩት እኔ አየዋለሁ ይህ ሁሉ ሕዝብ እንዲሰበሰብና የኦሪትን የነቢያትን የመዝሙርንና የወንጌልን የመልክቶቹን ሚስጥር ለመመርመርና ለማስተማር መላኬ የማይካድ ነው ። እውነትን ክህሰት ለይቶ ማወቅና ማስተማር ሰውን ያስደስታል እንጅ ሰውን አያተራምስም የሚተራመስ ካለ ሰውን የሚያተራምሰው ኃጥያቱ ብቻ ነው ። በክህዲነትህ ሞት ይገባሀል ለምትሉት ከሀዲ ለመሆኔ ማስረጃ የላችሁም ። ያልታዘዘ ለመስራታችሁ ቁርአኑም ቢሆን ብሉይና አዲስ የሚመሰክሩት በላንተ ላይ ነው ። ግን ይህን የምትሰሩት በምህይምነት በመሆኑ ካልተዋችሁት በለው ሳይሆን በፈጣሪያችሁ አምላክ ፊት ሞት ስለሚፈረድባችሁ ከሞት ወደህይወት የምትመለሱበትን መንገድ እንዳስተምራችሁ መላኬን አረጋግጥላችኋለሁ ። ስለዚህ እሽ ብትሉ ብትታዘዙ መሀሪው ጌታ ምህረት ያደርግላችኋል እምቢ ብትሉ ግን ሞታችሁ በአምላክ ፈቃድ ሳይሆን በራሳችሁ ጨካኝነት መሆኑን መረዳት ያሻችኋል ሲሉ ለከሳሾችና ለሸህ አደም መልስ ሰጡ ።

ለሸህ ዘካርያስ መልስ ማረጋገጫ ከብሉይ ከአዲስ በከሳሹ በሸህ አደምና በተከሳሹ ሸህ ዘካርያስ እየተጠቀሰ አማርኛና አረብኛ የሚያውቅ ሰው ተፈልጎ



እንዲያውም በከሳሾች እየተነበበ እየተተረጎመ ጉዳዩን ዋግ ሹምና መኳንንቶቻቸው ካጠኑት በኋላ ቀጠሮ ተሰጥቶ ጉባኤው ሲፈታ ከአደባባዩ የዋለው እስላሙም ሆነ ክርስትያኑ ክርክሩን በየመሰለው ይፈርድ ነበር ። በዚህ አይነት ወሬው በመላ የዋግ ሹምን ግዛት አልፎ የጎንደርንና የትግራይን ክፍለ አህጉር አዳረሰው ።

በዚህ በቀጠሮው ጊዜ ውስጥ እነ ሸህ አደም በነሱ ክሰና በሸህ ዘካርያስ መልስ አሰጣጥ ያለውን ልዩነት በደንብ ተረድተው ስለነበር የክርክሩ ውጤት የማያመረቃ መስሎ ስለታያቸው ከችግር ላይ ወደቁ ። ምክንያቱም በተደረገው ክርክርና የተቃዋሚው ወገን ከቤቱ ሲነሳ ዘካርያስን ባገኘው እንሽሀአላህ በዚች ሰይፍ አንገቱን ቆርጨ የሆነው ይሁን ሲል የነበረውና ሲናጽር ሆነ መስኮብ ሳበውም ሆነ ውጅግራ የያዘው ሁሉ ባለወጨፎውም ጭምር እንዲት ጥይት ለዘካርያስ ማጥፊያ አጣለሁን ሲል የነበረውም ወደ ሰቆጣ ከተማ መጥቶ ሸህ ዘካርያስን አዘን በማድረግ አላህ አክበር ብለው ድምጻቸውን ሲያሰሙ ለሰግደት በሚደፉበት ጊዜ ለሸህ ዘካርያስ የተገለጠው እምላክ የሚሰሟቸውን ልብ ሁሉ በጠበጠው ። ስብከቱን ለመስማት ባእድ ዘመድ ወዳጁ ጠላቱ ባንድ የሚሰበሰቡት አሜን አሜን ስለሚሉ ቢቻል በክርክር ባይቻል በጠብ ህይወቱን እናጠፋና እናርፋለን ሲሉ ያቀዱት እንዳልሰራላቸው ተረዱት ። እንዲሁም ለጠብ መጥተው ከነበሩት ብዙወቹ ወደ ሸህ ዘካርያስ እየቀረቡ እኛ ወሬ ስንሰማ ያላህ ጠላት ተነሳ ተብሎ ነበር የተነገረን ። አሁን ግን ነገሩ ተዛውሮ ያላህ ወዳጅ መሆነወን በስብከተወና በተከሰሱ ጊዜ በሰጡት መልስ ተረድተናል ስለዚህ በሚያስተምሩት ትምህርት ለመመራት አባባችንን ቆርጠናል ብለው አረጋገጡላቸውና የሳቸው ደቀመዝሙር ሆኑ ።

በዚህ ጊዜ ከሳሹ ሸህ አደምና ግብረአበሮቹ በጣም ተበሳጩና አሁንም በያገሩ ያሉትን እስላም ሁሉ በቀጠሮው እንዲሰበሰቡና በክርክሩ ካልተከናወነ በችሎቱ ወይንም ችሎት ምላሽ አደጋ ለመጣል እቅድ ተዘጋጀ ። ዳሩ ግን ሸህ ዘካርያስ ደጋፊወች እንደተቃዋሚወቻቸው አንገቱን በዚህ ሰይፍ ነው ቆርጬ የምጥለው እያሉ ሲናገሩ ስለነበር እረዳቶቻችን ናቸው ብለው እንዲረዷቸው እቅዱን አንድ በአንድ አስረዷቸው ። የሸህ ዘካርያሰ ደጋፊወችም እነሸህ አደምን መስለው እቅዱን ካወጡ በኋላ በሚስጥር እቅዱን ለሸህ ዘካርያስ አስጠኗቸው ። ሸህ ዘካርያሰም በቂ ማስረጃ ካገኙ በኋላ ለዋግ ሹም ጓንጉል የተጨበጠ ማስረጃ አቅርበው እቅዱን አስረዷቸው ። ዋግ ሹም ጓንጉልም በተረዱት መሰረት በጥብቅ ሲከታተሉ በሚስጥር የሸህ ዘካርያስ ደጋፊ ሲሆኑ የነሸህ እደም ረዳት በመምሰል የስለላ ተግባር የሚያከናውኑትን እስላሞች የሚቆጣጠሩ ሌሎች የዋግ ሹም ጓንጉል ወዳጅ የሆኑ እስላሞች የነሸህ አደም እረዳቶች መሰለው ሂደው እነሸህ አደምን ዋግ ሹም ጓንጉል እናንተን እንዲደግፉ እኛ እንለምናለን መቸም በክርክሩ አልሆነላችሁም ግን እንደማንም ብሎ የሸህ ዘካርያስን ህይወት ማጥፋት ነው ከዚያ ወዲያ ተከታዩ ሁሉ ይበተናል ወንጀል የሚፈጽመውን ሰው እንደማንም ብለን ደብቀን አርቀን ብናስቀምጠው መቸም ብርቅና ድንቅ ካለሳምንት አይደንቅ ካራት ካምስት ዓመት በኋላ ነገሩ ይረሳል የዚያን ጊዜ እንደልቡ ሊሆን ይችላል አሏቸው ።

እሁንም እነሸህ አደም ሌላ እረዳት ያገኙ መስላቸውና ያቀዱትን ተንኮል ዝርዝር አድርው ስላስረዷቸው ጉዳዩን ዋግ ሹም ጓንጉል በቀላሉ



ደረሰበት ። ለነሸህ አደም ሚስጥር መጠበቅ ያዳገታቸው ሁሉም እስላም ሁሉም ሶላት ሰጋጅ ሆኖ ወዳጆቻቸውንና ጠላቶቻቸውን ለይቶ ማወቅ ስለቸገራቸው ለሸህ ዘካርያስና ለዋግ ሹም መልክተኞች ሚስጥራቸውን ገልጸው በማስረዳታቸው ነበር ። በዚህ አይነት ለአንድ ወር ያህል ክቆዩ በኋላ ቀጠሮው ቀን ደረሰ ።

<u>ሁለተኛው ጉባኤ</u>

በተወሰነው ቀን አሁንም ክርክሩንና ውሳኔውን ለማስማት ከዋግ ሰዩም ግዛት ብቻ ሳይሆን ከትግሬ ከወሎ ከጎንደር አጅግ በጣም ብዙ እስላም ተሰብስቦ የሰቆጣን ከተማ ሞልቶ በከተማው ዙሪያ ድንኳኑን እየተከለ ይህን ጊዜ ይጠባበቅ ነበረ ። ዋግ ሰዩም ጓንጉል ሸህ ዘካርያስን አስጠርተው የገጠምክው ጦርነት ለህያላን ነገሥታት ለነአፄ ቴወድሮስ ለነአፄ ዮህንስ ያዳገተውን ነው ። ነገር ግን አለምን በውህ ሲያጠፋ ለኖህ ማምለጫ የሰጠ አምላክ ለሙሴ ባህሩን ከፍሎ በደረቅ ያሻገረ አምላክ ሲድራቅ ሚሳቅ አብድናጎን ክሳት ህይል ያዳነ ዳንኤልን ከአናብስት አፍ ያዳነ አምላክ አንተንም ከነዚህ ሊውጡህ ካሰቡት ያድንህ እኔና መኳንንቶቸም የቻልነውን ያህል ህይወትህን ከአደጋ ለመጠበቅ አንጥራለን ። እንዲያውም ክስ ካቀረቡ በኋላ በህግ በመከራከር ፈንታ አደጋ ስመጣል የታቀደውን አንድ ባንድ ስለደረሰኩበት የተነሱበት አላማ ውድቅ መሆኑን እኔና መኳንንቶቸ ተረድተነዋል ። አሁንም እቅዱ ከስራ ላይ እንዳይውል በልዩ ዘዴ ተከታትለነዋል ። ቢሆንም አንተም ደህና ደህና ጎበዞች የጦር መሳርያ ሰይፍ የያዙ አስከትለህ እራስህን ለመጠበቅ ሞክር አሏቸው ። እና በማግስቱ ዋግ ሰዩም ጓንጉል መኳንንቱና ታላላቅ ነጋዴወች ልዩ ልዩ ያደባባይ ሰዎችን ካህናትንና

እንዲሁም እያሌ የስላም ሸሆችን አስጠርተው ለጉባኤ ተቀመጡ ::

ከሳሹ ሸህ አደምና ተሳሹ ሸህ ዘካርያስ ወደችሎት ሲመጡ በብዙ ሸህ የሚቆጠር ሕዝብ አደባባዩን ስለሞላው ችሎት ወደተያዘው ስፍራ የጦር መሳርያ የያዘ እንዳይቀርብ በተደረገው ቁጥጥር በተሰይ ለአደጋ የተዘጋጀው ሰው ሽጉጡን በጀ ጠባቡ ውስጥ ታጥቆ አራሱን እንደሸሆቹ አንዘርፍፎ ሰላማዊ ሰው መስሎ መጣና ወደ ችሎቱ አገባለሁ ሲል ዘበኛው በልዩ ምልክት አውቆት ተመለስ ቢለው አልመለስም አለ ሁሉ እየገባ ለምን እኔ አክለከላለሁ ሁሉ ወንጀለኛ አይደለም አንተ ግን ወንጀለኛ ነህ መሳርያ የያዘ ወደ ችሎት አይገባም ተብሎ የታዘዘው በመተላለፍ በጀ ጠባብህ ውስጥ ሽጉጥህን ታጥቀህ ጋቢ ደርበህ አራስህን ሸህ አስመስለህ ሰላማዊ ለመምሰል ጠምጥመህ በልዩ ዘዴ የመጣኸው አንተ ነህ ብሎ ለቀም አድርጎ ሲይዘው ከአስር በላይ የሚሆኑ ወታደሮች ተሰብስበው ዘርጥጠው ጥለው ልብሱን ሁሉ ሲቀዳድዱት በደንብ የተዘጋጀው ጎበዝ በልብሱ ውስጥ የታጠቀው ሽጉጥ በሙሉ ጥይት ጎርሶ ተገኘ ወዲያው ችሎት መጀመርያ የተያዘው ሽጉጥ ተወርሶ ወህኒ ቤት እንዲሄድ ታዘዘና ዋናው ችሎት ተጀመረ ::

እነሸህ አደም ሸህ ዘካርያስን እንዲህ ሲሉ ወነጀሏቸው :: ሸህ ዘካርያስ እስላም ሲሆን የእስላም ሸርያና የእስላም ዲን ሊንድ እስላሙን ሕዝብ ስላም እየነሳ አስቸግሯልና ስለዚህ በሸሬያችን በዲናችን ልንፈርድበት ልንፈርድለትም የሚገባን እኛ ነን የክርስቲያን ዳኛ የእስላምን ሃይማኖት ስለማያውቀው ስልጣኑ ለኛ ይሰጠን ሲሉ አመለከቱ ::



ሸህ ዘካርያስም እስካሁን የኔን መብት ነበር የሚጋፉት አሁን ደግሞ የዋግ ስዩምን ስልጣን ወሰጀ የፈለግሁትን አደርጋለሁ ይህም አቤቱታ የነሸህ አደም አላማ ምን እንደሆነ ያስረዳል ሌሊት ሰው ለመግደል ሲስማሙ ያድራሉ ቀን እንደህግ ጠባቂ ሆነው ሰው ይከሳሉ :: ካሉ በኋላ ሸህ አደም ለማስተባበል ሞከር ሲያደርጉ :: ቆይ ላስረዳህ አሉና ሸህ ዘካርያስ አንድ ሁለት ሶስት ጊዜ የተሰበሰቡበትን ስፍራ በመጥቀስ ማን ምን እንደተናገረ ከመጀመርያ እስከመጨረሻ የሸህ ዘካርያስን ህይወት ለማጥፋት የታቀደውን አቅድ አንድ በአንድ ተንትነው ካስረዱ በኋላ እናንተ ሰው አያየንም ብላችሁ ትመክራላችሁ ምክራችሁን ጌታ ይገልጠዋል ይህም የራሳችሁ ፍላጎት አገልጋይ እንጅ የአላህ ሰዎች አለመሆናችሁን አሁንም የዋግ ሰዩምን አደባባይ በደም ልትበክሉት የታሰበውን ሥራ አላህ ገለጠው :: ጥይት የጎረሰው ሽጉጥ ተግባሩን ሳይፈጽም ተያዘ በተተኮሰ ኑሮ አንተንና ግብረአበሮችህን ይመታ ነበር እንጅ ሌላ ሰው አይመታም ነበር ነገር ግን አለመተኮሱ አላህ የንስሀ ጊዜ እንደሰጠህ እወቀው :: የተከበሩት ዋግ ሹም በቀረበብኝ ክስ በቂ መልስ ሰጥቻለሁ በዚሁ መልስ ይሰጠኝ እንጅ እነሱ ዳኛ እነሱ ባላጋራ ሆነው እኔ ተከሳሽ ከስልጣናቸው በታች ልወድቅላቸው አይገባም አሉና መልስ ሰጡ ::

## ውሳኔ

ቀጠሮው ለውሳኔ ስለነበር ፍርድ አዋቂ መኳንንት ተመርጠው በዋግ ሹም ወንበር በስተቀኝ አስር በስተግራ አስር እንዲቀመጡ ሆኖ ከነዚህ ሌላ ሶስት ፍርድ አዋቂ የዋግ ሹም ወንበሮች ከዋግ ሹም ወንበር አግርጌ በስርአት ተቀምጠው ነበር ::

የክርክራቸውን ጭብጥ መካከለኛው ዋና ወንበር ለተቀመጡት መኳንንት ዘርዝረው ካስረዱ በኋላ ፍርድ እንዲጀመር ትዛዝ ሰጥተው ተቀመጡ ።

አጋፋሪውም ከመካከል ቆሞ ከስተቀኝና ከስተጋሻ እያስነሳ በስርአት የተቀመጡትን መኳንንት ያስፈርድ ጀመር ። ከመኳንንቱ መካከል ተራቸው ሲደርስ ብድግ ብለው ኩታቸውን ከወገባቸው ላይ ሸንፈጥ ያደርጉና እንዲነሱ በዘንጉ ወዳመለከታቸው አጋፋሪ ተንደርድረው ወርደው ፊታቸውን ወደ ዋግ ሰዩም ዘወር ብለው ይቆሙና ባደላ ሳይ ይደላበት ባመጻኛ ሰይፍ ሞት ይታዘዝበት ካብ ይናድበት ወገን ይነሳበት ባደላም ይደላብኝ ። በሸህ ዘካርያስ ላይ በነሸህ አደም የቀረበውን ስሰማ ስርአታችንን አፍርሰሀል ወግ ልማዳችንን አስቀርተሀል ሃይማኖታችን ለውጠሀል በዚህ አይነት ሕዝቡን ሰለምታተራምሰ እንዳንተ ያለው ከሀዲ በጠቅላላው ሕብረተሰብ የማትፈለግ ሰው ነህና በሞት ትቀጣለህ የሚል በመሆኑ ተከሳሹ ሸህ ዘካርያሰ የሰጡት መልስ እኔ ያፈረሰሁት ስርአት ላላህ ስርአት ተቃራኒውን ነው ። ልማድም ባሰቀር የማይገባውን እንጅ ተገቢ የሆነውን አይደለም ። ሃይማኖት ለውጠሀል ለምትሉት በልበ ወለድ የተያዘውን እንጅ እውነተኛ ሃይማኖት አልለወጥኩም በማለት መልሰ ሲሰጡ ከጌታ የታዘዝኩትን በማስተማሬ እንደከሀዲ ተቆጥሬ በሞት እንድቀጣ ሊፈረድብኝ አይገባም ብለዋል ።

አሁንም የሸህ ዘካርያስ መምህርነት የረቀቀና የተደነቀ ሊከበር የሚገባው መሆኑን ለማስረዳት ያህል በጠብ መልክ በወሬ ክፋቅ የመጡት በቅርብ ሆነው የጸሎታቸውንና የሰብከታቸውን መልክት ሲሰሙ የመጡበትን ሀሳብ ለውጠው የሳቸው ተከታይ ለመሆን



ቃላቸውን የሰጡ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ናቸው ወንድሞቹ ክሳችሁ ወግን አለው ወይስ አግባብ ? ይህን የመሰለ የጊዜውን ነብይ ካምላክ ተልኮ ለኛ ቢሰጠን እንግደለው ብሎ ፍርድ መጠየቅ የማይገባ በመሆኑ የተከሰሱበት ወንጀል ውድቅ ሆኖ የሸህ ዘካርያስ ትምህርት እንዲስፋፋ ሲደረግ ይታየኛል እያለ ይፈርድ ጀመር ።

በዚህ አይነት እየዘረዘሩ በቀኝና በግራ የተቀመጡት መኳንንት ከፈረዱ በኋላ አሰቀድመው የቀኙን ወንበር ሁለት እጆቹን ወደዳኛው ዘርግቶ ተራው የሳቸው መሆኑን አጋፋሪው ስላመለከታቸው ብድግ ብለው ተነስተው የማእረግ ልብስ ካባቸውን እንደደረቡ አድሳዊ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ የተለመደውን በመናገር ከገለጹ በኋላ ያባቶች ተረት የመጽሐፍ አረቂ ነው ይባሳል ። ተከሳሽ የሚመልሰውን ከሳሽ ቢያውቅ ኖሮ በመክሰስ ፈንታ አርፎ ይቀመጥ ነበር ይባላል ። አሁንም አጥፊ ነው በሞት ይቀጣል ብሳችሁ በክሰሳችሁት ምክንያት ባለስልጣን ክሱን ለጉባኤ ሲያቀርበው አጥፊ አለመሆኑን ከማስመስከሩም በሳይ እንዲያውም ይህ ክስ ሊቀርብበት የቻለው የሸህ ዘካርያስ ትምህርትና ህይወት ያበራው ብርሃን የናንተን ተንኮልና ጥፋተኝነት ገልጦ ሰላሳየባችሁ ብርሃኑን አጥፍቶ በጨለማ ለመሰወር የታቀደ ነው ። ይህንንም ለመረዳት የቻልነው በፍርድ ጠይቆ ውሳኔ ሳያገኙ በኃይል ለመጠቀም በተደረገው ሙከራ ነው ። ስለዚህ ክሳችሁ ውድቅ ሆኖ እናንተም የታዘዘውን ትታችሁ በልበወለድ ለስጋችሁ የሚመቻችሁን ብቻ ስትሰሩ ስለኖራችሁ ለወደፊቱ ትክክለኛውን መንገድ ሊቀ ሊቃውንቱ በሰው ሳይሆን ሚሰጥረ መለኮት የተገለጸለት ሸህ ዘካርያስ ሲያስተምራችሁ ይታየኛል እንጅ ሊሞት አይገባውም ብለው ፈርደው ተቀመጡ ።

አሁንም አጋፋሪው በስተግራ የተቀመጡትን ዳኛ /ወንበር/ ፈንታው የሳቸው ስለሆነ ተነስተው እንዲተቹ ስለጋበዛቸው ተነስተው ከቆሙ በኋላ እካስ ያለ ታግሶ እጸድቅ ያለ መንኩሶ ነው ይባላል እጥፌ ነህ በሞት ትቀጣለህ ብሎ ክሶ አደባባዩ ሳይለወጥ እራስ ቢያጠፋ መገኘት በጣም የሚያሳፍር ጉዳይ ነው ። እንዲያውም ጉዳዩን ጠለቅ ብለን ስንመለከተው ምህይማን በሊቁ ላይ ክስ ማቅረባቸውን በቀላሉ ተረድተነዋል ። ስለዚህ ያቀረቡት ክስ ውድቅ በመሆኑ በነጻ ተለቀው በትጉህነታቸው የተማሩትንና በመንፈስ ጌታ የገለጸላቸውን ሚስጥረ መለኮት በሙሉ ነጻነት እንዲያስተምሩ ሲፈቀድላቸው ይታየኛል ብለው በመተቸት ፈርደው ተቀመጡ ።

አሁንም አጋፋሪው የመካከለኛውን ዳኛ ዋናውን ወንበር እጅግ ትህትና በተሞላበት አገባለጽ የድርሻቸውን እንዲተቹ ጋበዛቸውና ። ብድግ ብለው ተነስተው የጌታየን ጠሳት የቀረበውን በሰይፍ የራቀውን በመድፍ አርዶ ፈርዶ ይጣለው ። ፍትህ እርት ይጠበቅ ። አመጻኛ ይውድቅ ። ፍርድ ለልጅ የሚያልፍ ያባቶች ቅርስ ነው ። እኛ ዛሬ ጊዜ ሰጠን ብለን ብናደላ ሰው ነንና ነገ ስልጣናችን መወሰዱ ባለመቅረቱ ለቆየው ታሪክ ቅን ፍርድን ብናቆይ ልጅ ምስክር ነው ። አሁን የቀረበልን ጉዳይ ክስ ያቀረቡት እነሽህ አደም ሽህ ዘካርያስ ጥፋተኛ ነው ሞት ይገባውል የሚል ሲሆን ግን ጉዳዩ ሲጠና ተከሳሹ ተበዳይ ከሳሾቹ በዳይ ሆነው መገኘታቸው ጅራፍ እራሷ ገርፋ እራሷ ትጮሀለች እንደሚባለው መሆኑ ነው ። ሽህ ዘካርያስ በተከሰሰብት ነገር ሁሉ ፈጽሞ ንጹህ ሆኖ በመገኘቱ ክሱ ውድቅ ነው እንዲያውም ክስ ባቀረቡበት አደባባይ ላይ እራሳቸው ወንጀል ለመስራት ያቀዱት ሴራ እንዴት እንደተገለጸ



ሲታሰብ ለጥፋታቸው ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገባ ነው ። ስለዚህ ሽህ ዘካርያስ ከዛሬ ጀምሮ ለስራው ሙሉ ነጻነት አግኝቶ እንዲያስተምር ሲፈቀድለት ይታየኛል ። ብለው ፈርደው ተቀመጡ ።

በመጨረሻም አጋፋሪው በትህትና መሬት እስኪነካ እጅ ነስቶ ይድረስ ብለዋል ባለግዜ ፍርድ ለመፋረድ ዋግ ስዩም ጓንጉል ከወንበራቸው ሲነሱ ጉባኤው በሙሉ ብድግ ብሎ ተነሳ ።

አሁን ይህ ሁሉ ሕዝብ እየተሰበሰበ ሁለት ጊዜ ጉባኤ አድርገን ጉዳዩን ያጠናነው እራሳችሁ አቤት በማለት ፍት እርት ጠይቃችሁ መልሳችሁ የሃይማኖት ዳኝነት ለኛ ይገባል ብላችሁ ስልጣናችንን ለመንጠቅ አስባችሁ ይህንም እንደማይከናወን ስትገነዘቡ ሌላ ያመጽ ሴራ አዘጋጃችሁ ። በዚህም ሳይከናወንላችሁ ቀርቷል ። እንዲያውም በወሬ ሲሰሙ ለክስ ሲቀርቡ ጉዳዩ መልኩን ስለለወጠባቸው ዘካርያስን ለመከተል ሀሳባቸውን የቆረጡ ብዙወች መሆናቸውን እራሳችሁ ታውቃላችሁ ። ፍርድና ሞት በግድ እንጅ በውድ አይደለም የሚመጣ ትክክለኛ ፍርድ የሚገባ ከሆነ የሞት ቅጣት ለናንት ይገባል እንጅ ለዘካርያስ አይደለም ግን እየታገስናችሁ ከዚህ ደርሰናል ።

በተማረው ቅዱሳን መጽሐፍት ሆነ በተገለጸለት መንፈስ የአምላክ አገልጋይነቱ በማንም ህሊና ተቀባይነት እንዳለው እራሳችሁ ጭምር በዚህ ነገር ፍረዱ ብላችሁ ከኛ ጋራ እንደምትስማሙ እርግጠኛ ነኝ ። እንደምትሰሙት ሁሉ ጉባኤው በአንድ ድምጽ ፈርዶባችኋል ። ህሊናን መቃወም ይቅርታ የለለው ኃጥያት ነው ። በህገራችን በኢትዮጵያ ብዙ ልዩ ልዩ

ሃይማኖት ያላቸው የሃይማኖታቸውን ጉዳይ ለየግላቸው አርገው ስለሀገራቸው ያላቸው አስተያየት አንድ በመሆኑ ተደጋግፈው ሲኖሩ ታያላችሁ ። እላንት ወንድማማች ስትሆኑ ይህን ያህል የጥላቻ መንፈስ በመካከላችሁ ሊገኝ አይገባምና ለዘካርያስ እንኳን ሞት ቁንጥጫም አይገባው እንዲያውም ሹመትና ሽልማት ነው የሚገባው ። በግዛታችን ይህን ያስጀመረው አምላክ ስራውን እንዲያከናውንለት እንመኛለን ። በምናስተዳድረው አገርም በሙሉ ነጻነት እንዲያስተምር ፈቅደንለታል ። ትምህርቱንም በመላው ኢትዮጵያ እንዲያሰራጭ ጽኑ ምኞታችን ነው ። በዘካርያስ ላይ አደጋ እንዳይደርስበት እነ ሽህ አደም አምስት ዋስ እንዲጠሩ ይሁን ። በተሰጠነው አደራ ፈርደን ከሳሽ ተከሳሽን አስናብተናል ሲሉ ጉባኤው ተፈታ ። ሽህ ዘካርያስም የተከሰሱበት ጉዳይ በሰላም አልቆላቸው ለማስተማር ሙሉ ነጻነት ስለተፈቀደላቸው ከጉባኤው ሲመለሱ እግዚያብሔር አብሯቸው መሆኑን ሕዝቡ እንዲያውቀው ግርማ ሞገሱን ቅዱስ መንፈሱን አጎናጽፏዋቸው ነበር ። እንኳን ሊደግፍዋቸው ወደ ሰቆጣ የመጣው ይቅርና ሊቃወማቸው የመጣው እንኳ ከሳቸው እንለይም እኛም እየተከተልን ይህንን ጸጋ እንካፈላለን እያለ ሀሳቡን ቆርጦ የጸናው ቁጥሩ ከሽህ አለፈ ። ሠራዊቱን በብዛት ማስከተሉ አዳጋች መስሎ ስለታያቸው ከትግሬ የመጣውን ሕዝብ ወደ ትግሬ እንዲመለስ ምክር ለጥተው አህመዲን የተባለውን ተማሪያቸውን የመምህርነት ስልጣን ሲኖረው የሚችል የተፈጥሮ ችሎታም ያለው መሆኑን ስለተመለከቱ ወደ ትግራይ ሄዶ እንዲያስተምር ነገሩት ። እርሱም በብዙ መቶ የሚቆጠሩትን ደረሶች አስከትሎ ወደ ትግራይ ሄዶ አድዋ ላይ ማስተማር ጀመረ ።



ሽህ ዘካርያስ ከዋግ ሹም ጓንጉል ተሰናብተው ወደ ቤታቸው ወደድህና ጉዞ በጀመሩ ጊዜ እጅግ ብዙ ሠራዊት ይከተላቸው ጀመረ የትግሬን እንዳሰናበቱ ሁሉ ሁሉንም በየመጣበት እንዲመለሱና በተቻላቸው እየተዘዋወሩ እንደሚያስተምሩ እራሳቸው በየአውራጃው እየተዛወሩ ለማስተማር ቢያቅታቸው ከፍተኛ ትምህርት ያላቸውን እየመደቡ የሚልኩ መሆናቸውን ስለገለጹላቸው አያሌው ሕዝብ ወደየመጣበት አውራጃ ተመለሰ ። እርሳቸውም ከሰቆጣ ተነስተው አመድ ወርቅ ከተባለው አውራጃ ከተማ በደረሱ ጊዜ ብዙ ዘመዶቻቸው አረትተው በመመለሳቸው በልዩ ልዩ ስጦታና ብዙ ድግስ እያደረጉ እርሳቸውንና ተከታዮቻቸውን በመቀበል ደስታቸውን ገለጹላቸው ። እንዲሁም አመድወረቅ ሆነው ወደ ቤታቸው ወደላማ የሚመጡ መሆናቸውን አስቀድመው ልከው ኑሮ ቤተሰቦቻቸውና ጎረቤቶቻቸው እጅግ ብዙ ድግስ ደግሰው ለመቀበል ሲጠባበቁ ከአመድወርቅ ተነስተው ሲልዳን አቋርጠው ላማ ከቤታቸው በደረሱ ጊዜ በጣም ደስታ ሆነ ። የተደሰቱበት ምክንያት ቀርቦባቸው የነበረው ክስ ያስሞትህል የሚል ስለነበር ክሱ ውድቅ ሆኖ ፍርዱ ለሳቸው ከመሆኑም በላይ እንዲያስተምሩ ፈቃድ መቀበላቸው ለወዳጅ ለዘመዱ ሁሉ ተጨማሪ ደስታ ሆኖ ነበር ። ለጥቂት ጊዜ እረፍት አርገው በቆዩበት ጊዜ አንድ አስደናቂ ነገር ደረሰ ። በዚህ ነገር የአምላክ ፍርድ ብዙ ትምህርት የሚሰጥ ነው ግን ለጊዜው ለወላጅ ለዘመዱ በጣም ያሳዝናል ሲሉ ተናገሩ ። ይህም የወርቅነህ መሐመድ አሟሟት ነበረ ። እርሱንም በሚቀጥለው ምእራፍ አቀርበዋለሁ ።

ታናሽ ወንድም ምክንያቱ ባልታወቀ ጉዳይ እራሱን ባሞሌ ጩው ፈነከተውና ደማ ። አቶ እረቂ ንጉሤ ወንድሙን የፈነከተውን ሰው በሰይፍ አመታለሁ ብሎ ሲበነዝር ወርቅነህ ሙሐመዴ ሚዜውን እስጥላለሁ ብሎ ሲገለግል ከሚዜወቹ ላንዱ የተሰነዘረው ለወርቅነህ ሆንና ሰይፉ ከወርቅነህ ሙሐመዴ ግንባር አንድ ጣት ያህል ጠልቆ ገባ ። ለጊዜው ለመናገር ሳይከለክለው ስለቆየ አቶ አረቂ ንጉሤን በደም እንዳትፋረዱት እኔን ለመግደል አላሰበም ነበር ለሌላው የታሰበው ደረሰኝ እንጅ ብሎ ተናዞ ወርቅነህ ሙሐመዴ ወዲያው ከቤቱ እንደደረሰ ሞተ ። ገና የሙሽራውና የተከታዮቹ ጉዳይ ወሬው ሳይመጣ ሸህ ዘካርያስ ከመንደራቸው ወደምታለቅሰው እናት ሄደው ሁናቴውን ከተመለከቱ በኋላ ይህች ልበቅን እናት ክፉውንም መልካሙንም የሚገልጽላት የአላህ ሚስጥር ተካፋይ ናት ብለው እንባቸውን ካፈሰሱ በኋላ በሉ ታገሱ ምንም ለናንተ ለወላጆች አላዛኝ ጉዳይ ቢሆን ብዙ ትምህርት የሚገኝበት ሚስጥር ነው ብለው በመናገር ሞሚና ይመርን እጽናንተው ከተቀመጡ በኋላ በርግጥም ቀኑ ሲመሽ ሚዜወቹ ወርቅነህ ሙሐመዴን በወስካ ተሸክመው ዘለቁና የበርጉ ሰፈር በሐዘን ተበከለ ።

ከዚህ በላይ የጻፍኩትን ታሪክ የነገሩኝ ከሚዜወቹ አንዱ በነበሩት የወለዱኝ አባቴ በአለቃ ንጉሤ ቦጋለና በወርቅነህ ሙሐመዴ ልጆች በተበጀ ወረቅነህና በኃይሉ ወርቅነህ ነው ።

ይህ በሆነ በማግስቱ የሟች ወንድም አቶ ሃሽም ሙሐመዴ ነፍስ ገዳዩን ሰው በዳኛ አስይዘው አቀረቡትና ባለስልጣኑ ጉዳዩን በሚያጠኑበት ጊዜ የገዳዩ የእቶ እረቂ ንጉሴ እናት ለሞሚና ይመር ሳንች ለድህይቱ ልጅ ብለው ልጄን የሚገሉት ይመስልሻል ? አሉ ። ሞሚና ይመር ደግሞ በኔ ልጅ ምክንያት ልጅሽ እንዲሞት አልጠይቅም ምክንያቱም ልጄ ሲናዘዝ እኔን ለመግደል አስቦ ስላልገደለኝ ለሞት እትፋረዱት ብልዋልና ግን ስላንች የግፍ አነጋገር የሁላችን ፈጣሪ



የሚሰጥሽን ፍርድ ታያለሽ ፍርዱም እንደኔ ልጅሽን ሰው ገሎት የልጅ ሐዘን በተለየ ሰው ሲገለው ስሜቱ ምን ምን እንደሚል ትቀምሽዋለሽ። ልጅሽም አረቂ ንጉሤ ወንድሙን ሰው ገሎበት እንደ ልጄ ሐሽሜ የወንድም ሞት ምን ምን እንደሚል ስሜቱ ምን ምን እንደሚል የሚቀምስበት ጊዜ እሩቅ አይደለም ሲሉ ተናገሩ ። በዚህ ጊዜ ያገር ሽማግሌ ለወርቅነህ ልጆች ማደጊያ የነብስ ዋጋ አረቂ ንጉሤ እንዲከፍል ወሰነው ሰላስታረቋቸው አረቂ ንጉሤ የነብስ ዋጋውን ከፍሎ ወደ ቤቱ በተመለሰ ጊዜ ብዙ ሳይቆይ ከታናሽ እህቱ ባል ጋራ ተጣልቶ ገላጋይ ሁለቱን ይዞ በሚገለግልበት ጊዜ እንድ ጊዜ ጠብ እንስቶ ከስርጉ በአሞሌ ጩው እራሱን በመፈንከቱ ለወርቅነህ ሙሐመዴ ሞት ምክንያት የሆነው ያረቂ ንጉሤ ታናሽ ወንድም ለወንድሙ እረድቶ የህቱን ባል በዱላ ሊማታ ገስግሶ ሲቀርብ የእህታቸው ባል ጠብመንጃ ይዞ ስለነበር ተኩስና ግንባሩን ቢያፈርሰው ባሞሌ ጩው የተጀመረው ጭንቅላት አሁን በጠብመንጃ ስለታረሰ ያረቂ ታናሽ ወንድም ተዘርሮ ወደቀ ። እናቱ ልጄ ልጄ እያለች ስታለቅስ ልጇም አረቂ የናቴ ልጅ እያለ ያለቅስ ጀመር ። በሰው ቤት ያቀለሉት ሐዘን በነሱ ቤት ወድቆ እያሌ ልጆች የወለደው የልጃቸው ባል ልጃቸውን ገሎት እነሞሚና ይመር ይህን እንኳ አስቀድመው በራእይ እንዳዩ ቢናገሩ በባላጋራቸው ሳይታመን ከቆይ በኋላ በተግባር ላይ በዋለ ጊዜ በስፈሩት ቁና መሰፈር እንደማይቀር ተረዱት ።
ጉዳዩ በዚህ አላበቃም ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲተካ የወርቅነህ ሙሐመዴ ልጆች አራዳች ወርቅነህና ተበጀ ወርቅነህ አባቱ ሲሞት ተረግዞ የነበረው ሀይሉ ወርቅነህ ተወልዶ ሶስቱም አደጉና ተበጀና ኃይሉ ጠብመንጃ ይዘው በጌምድር ተሻግረው ቆይተው ወደ ድህና ሲሻገሩ ተክዜ ላይ ሰፈራ አድርገው ሳለ ከበለሳ ወደ ድህና የሚሄድ

አንድ ሽማግሌ ከጓደኞቹ ጋር መጥቶ ከነተበጀ አጠገብ ሰፈረና ተበጀ ወርቅነህን እባክህ ልጄ በዝች ቅል ከጥላ ስፍራ ውሀ ቀድተህ አምጣልኝ ብሎ ጠየቀው ተበጀም እሽ ብሎ ውሀውን ሊያመጣ ወደ ወንዙ ሲሄድ ሽማግሌው ማን መሆኑን የሚያውቅ ከሰፈር ካሉት አንድ ሰው ተበጀን ተከትሎ ሄደና ውሀ አምጣልኝ ያለህን ሽማግሌ ታውቀዋለህ ወይ ? አለው ተበጀም ኧረ አላውቀውም አለው እባትህን የገደለው እረቂ ንጉሤ የሚባለው ይህ ነው ባትገለው እንኳ የሱ ውሀ ቀጅ ለምን ትሆናለህ? አለው እሱም አላወቀኝ እኔም አላወቅሁት ዳሩ ግን ባውቀውም ያባቴ ጉዳይ አያቴና አጎቴ ታርቀው ስለቆዩ እኛ ባባታችን ደም የመበቀል ስሜት የለንም ውሀውንም እሰጠዋለሁ አንተም ባልነገርከኝ ደግ ነበር ብሎ የቀዳውን ውሀ ወስዶ ሰጠው:: እብረው ያሉት ሰወች ለእረቂ ንገሤ ሁለት ባለጦር መሳሪያወች እሱ የገደለው የወርቅነህ ሙሐመዴ ልጆች መሆናቸውን ነገሩትና በቁሙ ሞተ :: ተበጀም የሰውየውን ድንጋጤ አየና ላረቂ ንጉሤ እንዲህ አለው እኛ እኮ ልንገድልህ ብንፈልግ እስከዛሬ አጥተንህ አይደለም ዳሩ ግን አስቀድሞ ያባታችን ኑዛዜ ሁለተኛ አያታችንና አጎታችን የታረቁት እርቅ ከጠቡም መነሻ አባታችን በጠብ ሳይሆን በገላጋይነት በመሞቱ ይህ ሁሉ የበቀል መንፈስ እንዳንከተል ስላገደን ነው ዝም ብለንህ የኖርነው :: እሁንም አትደንግጥ ብለው አጽናኑትና ቤቱን ሄደ :: የሚያስገርመውም ይህ ሰው በሰው መሞቱ የማይቀር ፍዳ መሆኑ ነው:: አሁንም ብዙ ከቆዩ በኋላ ጠላት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አምስት አመታት በቆየበት ጊዜ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ለአርበኝነት በተሰማሩበት ወቅት ተበጀ ወርቅነህ፤ ኃይሉ ወርቅነህና የእህታቸው ባል አለቃ ምትኩ የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ አሽከሮች ስለሆኑ በተለየ ተበጀ ወርቅነህ ድምጽ በጣም አስደሳች ስለሆነ እንዳባቱ ሲያቅራራ ሲሸልል



ፈሪ ያዋጋል :: የጠላት ጦር በከበደ ጊዜ ለቅቀን በጌምድር እንሻገር እያሉ ሲያስቸግሩ መኳንንቶቹ እንዲሁም ልጃቸውን ማሞ ኃይሉን ጠሳት ስለወሰደው

ተበጀ ሲያቅራራ

አባ መረብ ኃይሌ በለው ግፋ ግፋ ፤
ግልገል ይፈለጋል እንኳን ልጅ ሲጠፋ ::
እንልቀቅ እንሂድ ያሉቱ ፤
ወዴት ነው አገሩ የምንሞትበቱ ::
አባ መረብ ኃይሌ አልብሰኝ ነጠላ
አብላኝ አንድ እንጀራ ፤
ጉልበቴ ያንተ ነው ሲጋየም ያሞራ ::
አወይ ጠላት ሞኙ ሰራ ካፋፍ ላይ ፤
የማይበላ አዝመራ ይጠበቃል ወይ ::
አልቢኑን ለበኑን መድፉን መትረየሱን
አንተው ብትሰራው፤
በገዛ ጌታው ነው እንጨትም የሚያልቀው ::
አባመረብ ኃይሌ የጭንጫ በርበሬ ፤
ተጨነቀ ጠላት እየሰማ ወሬ ::
አባ መረብ ኃይሌን ወለህ ላይ ላየው ሰው ፤
እውልቆ ቀሚሱን እርሳሱን ሲለብሰው ::
ወለህ ከሜዳው ላይ እነማን ማን ዋሉ ፤
አባመረብ ኃይሉ የጦር ጀኔራሉ ::

እያለ እያቅራራ የጎበዝ ወኔ የሚቀሰቅሰው ተበጀ ወርቅነህ ከታናሽ ወንድሙ ከኃይሉ ወርቅነህና የእህታቸው ባል አለቃ ምትኩ ጋራ ሁነው ከደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ጋር ሳሉ አረቂ ንጉሤ ሽማግሌው ስቆጣ ሄዶ የጠላትን ጦር እየመራ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደን ለማስገደል ይዞ ወደ ድሀና መጣ። በተደረገውም ጦርነት የጠሳት ሠራዊት ድል ሁኖ አረቂ ንጉሤ ከስምንት

ጓደኞቹ ጋር ሁነው በምርኮኝነት ቀረቡና ስራቸው ሁሉ ተዘርዝሮ ለጦር ፍርድ ቀረቡ ። በዚህ ጊዜ አለቃ ምትኩ ፍትሀ ነገሥት አዋቂ ስለነበሩና እንዲሁም ኃይሉ ወራቅነህ የተማረ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው ስለነበረ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ፍረዱ አሏቸው ። እነ አረቂ ንጉሤ ከጧት እስከማታ የጥፋት ስዎች ናቸው ። ላገራቸው ጠላት በመደገፍ እናት አገራቸውን ቢክዱ ከጃችን ጥሏቸዋል ። አሁን ብንገላቸው እስ በሷ አፋጀኋት እያለ ጠላት ስለሚደሰት በሌላ ይቀጡ እንጅ በሞት አይቀጡም ብለው ስለፈረዱ ሌላ መኳንንት አገራቸውን ጌታቸውን የከዱ ለምንም አይጠቅሙ ይሙቱ በተደረገው ጦርነት ያለቁትን ወንድሞቻችን ደም እንበቀላቸው እያሉ ፈረዱ ። ደጃዝማች ኃይሉ ግን ስጠላት ወገኖቼን በመግደል አላስደስተውም ብለው በእስር አስቀምጠዋቸው ። በኢሳያስ ምእራፍ 26 ቁጥር 9 ና 10 ፍርድህን በምድር ባደረግህ ጊዜ በዓለም የሚኖሩ ጽድቅ ይማራሉ ። ለኃጥያተኛ ብትራራ ጽድቅን አይማርም በቅኖች ምድር ክፉ ያደርጋል የእግዚያብሔርንም ክብር አያይም ። ይላል አረቂ ንጉሴም በፍርድ የተደረገላቸውን ምህረት ባያስቡበት እሁንም ጠላት በምን መንገድ እነደጃዝማች ኃይሉ ከበደን የሚያጠቃበትን እቅድ አዘጋጅተው ጽፈው ለጠላት ለማድረስ አስበው መልክተኛ ሲፈልጉ ከደጃዝማች ኃይሉ አሽከሮች የእስረኞቹ ወዳጅ መስሎ የቀረበውን የጻፉትን ደብዳቤ ለጠላት እንዲያደርስላቸው ስጡት ። እርሱም ለጌታው ስለስጠው የእስረኞቹ ሴራ ተገለጠ እንደገና እነ አረቂ ንጉሤ ለፍርድ ቀረቡና በስቅላት እንዲቀጡ ተፈረደ ። ተበጀ ወርቅነህና ኃይሉ ወርቅነህ ባሉበት አረቂ ንጉሴ የአባታቸው ገዳይ አይናቸው እያየ የሚታነቅበትን ገመድ ካንገቱ ሲያጠልቅና ሽልው ሽልው እያለ ህይወቱ ሲያልፍ ተመለከቱ ። ይህንን ታሪክ የነገሩኝ እራሳቸው የታሪኩ ባለቤቶች ናቸው ።



ከዚህ ቀጥየ የዘረዘርኩት በወርቅነህ ሞት በሚል መነሻ ሸህ ዘካርያስ ምንም ለወላጆቹ ከባድ ህዘን ቢያደርስም የእግዚያብሔርን ፍርድ የሚያስተምር ሚስጥር ያለበት አብይ ነገር ነውና ብለው የተናገሩትን ለማስረዳት ነው ። ስለዚህ እንዲህ የተነሳንበትን የሸህ ዘከርያስን ታሪክ እንመለስና እንከታተል ።

ሸህ ዘካርያስ ላማ ሁነው የወደፊት ስራቸውን ለማስፋፋት ስቆጣ ከተማ የሚኖሩትን ተከታዮቻቸውን እነነጋድራስ አረጉትን፤ እነ አለቃ አረዳ፤ እነአለቃ ኃይለየሱስንና አለቃ ጴጥሮስን ወደ ፊት እንዲያስተምሩ የተላኩትን ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘሩትን ሰወች አደራ ብለው እሳቸው ወደ በጌምድር ተሻግረው ልጭ ከምትባል ቦታ ቡብናት ወረዳ ከምትገኝ ሄደው ተቀመጡ እና ማስተማር ጀመሩ ። ስለሸህ ዘካርያስና በበጌምድር ስለተፈጸመው ጉዳይ ከመጻፌ በፊት ባጭሩ ወደ ትግራይ በአህመዲን የሚመራው ተማሪና አህመድ ዲን የፈጸሙትን ላነሳ እወዳለሁ ።

## *ምእራፍ 10*

## *አድዋ ላይ የተጀመረ ስራ*

እህመዲን ወደ ትግራይ ሄዶ አድዋ ከተባለው ታሪካዊ ስፍራ ላይ ቁርአኑን ያስተምር ነበር ። ትምህርቱም ከመምህሩ ከሸህ ዘካርያስ እንደተማረው ሁሉ የቁርአኑን መነሻና ሚስጥር ከብሉይ ከህዲስ ኪዳን እንዲለይ ሳይሆን ለእንድ አላማ የተዘጋጀ ለመሆኑ እየዘረዘረ ሲያስተምር ቁርአኑን በሰው ቋንቋ ስለተጻፈ መርምሮ ባለማወቅ በልማድ የሚፈጸመውን ሁሉ እንደሕግ የሚቆጥሩትን አፈራረሰባቸው ። እነሱም በወሬ ሰምተውት የነበረውን አሁን እህመዲንና ጓደኞቹ መጥተው ማስተማር እንደ ጀመሩ ሲያዩ እህመዲንን ተው አታስተምር እያሉ ተቃወሙት ። እህመዲንም የቁርአኑን ቃል ጠብቁ ምነው በአወልድ ቃል እየሄዳችሁ ትስታላችሁ ያልታዘዘውን ትሰራላችሁ እያለ የሚሰሩት ሁሉ ያልታዘዘ መሆኑን ገለጸላቸው ።

ተቃዋሚወቹ ከደጃዝማች ገብረሰላሴ ላይ ከሰሱት። ክሱም ስቆጣ ላይ እንደተከሰሱት ሁሉ ሃይማኖታችን ለውጠህል ስርአታችንን አፍርሰህል ብለው ነው ። እህመዲንም ወደ ጉባኤው ቀርቦ መልስ ሲሰጥ ሃይማኖት እኛ አለወጥንም ግን እናንተ የተጻፈውን ትታችሁ ለስጋችሁ በሚመቻችሁ በመሄድ ያልተጻፈ የምትሰሩ እላንተው እራሳችሁ ናችሁ ። ለዚህ ሁሉ አስረጅ እሰጣለሁ ብሎ መለሰላቸው ። ደጃዝማች ገብረሰላሴም በቀጠሮው ብዙ ጉባኤ ሰብስበው በተጣራ ዳኝነት አጋጠሙና ጉዳዩን በእርጋታ አጠኑት ። በጉባኤውም ቀን ብዙ አረብኛና አማርኛ የግእዝ ቋንቋ የተማሩ ሰወች እየፈለጉ ጉዳዩን ሲያጠኑ ሰነበቱና በቀጠሮው እንደገና ሰብስበው በጠየቋዋቸው ጊዜ ነበልባሉ እህመዲን የዘካርያስ ደረስ የሚመልስለት ጠፋ ። ስለተከሰሰበት ሲመልስ የሰማው ሁሉ ሲደነቅ ደጃዝማች ገብረስላሴ እንዲህ አሉ ይባላል ተማሪያቸው ይህን ያህል ሊቅ ሲሆን እራሳቸው ሸህ ዘካርያሰ ቢመጡ



ምን ሊሆን ኑሮ ነው ይህ ሰው እውነተኛ የሃይማኖት ተክል ነው ። እውነት ሲመጣ ህሰት ሰፍራ የለውም ልማድ ዋጋ የለውም ትክክለኛ እውቀት በለለበት ጊዜ ብቻ ነው ብለው በመናገራቸው የእህመዲን ስም ከዚህ ቀን ጀምሮ ተክለሃይማኖት እየተባለ ይጠራ ጀመር ።

አንዳንድ መኳንንቶች ሽህ ዘካርያሰን ሰቆጣ ላይ ተከሰው በቀረቡ ጊዜ ያደባባይ መልሳቸውን ሰለጸሎታቸውና ስብከታቸው ሲናገሩ የሰማቸው ለደጃዝማች ገብረሰላሴ ሸህ ዘካርያስ አምላክ በሰልጣኑ ግርማ ሞገሱን ጸጋ መንፈሱን ያጎናጸፋቸው ንግግራቸው ለባለ ስልጣን ሆነ ለተራ ሰው፤ ለብርቱ ሆነ ለደካማ፤ ለህብታም ሆነ ለድሀ እኩል የሆነ በረከት የሚሰጥ በእውነት የእግዚአብሔር ሰው መሆናቸውን እየዘረዘሩ ነገሯቸው ። ላቀረቡለት ክስ የሰጠው መልስ ከብዙው በጥቂቱ እንደሚመለከተው ነው ።

የእስልምና ሃይማኖት መመሪያ የሆነው ቁርአን ራሱ ስለ ብሉይ ኪዳንና ሰለ ህዲስ ኪዳን እንዲህ ይላል ። እላንት የመጸሀፍ ባለቤቶች ሆይ ኦሪትና ወንጌልን ከጌታችሁ ወደ እላንት የወረደ እስከምታቆሙ እሰከምትሰሩባቸው ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው ምእራፍ 5 ገጽ 78 ኤል-ሚኢዳህ ክፍል 6 አንቀጽ 66 እሰከ 68 ተመልከት ።

እነዚህ መጽሐፍት ከየት እንደተገኙ በማን እንደተላኩ ቁርአኑ ሲያስረዳ ለሙሴ መጽሐፍትን በእርግጥ ሰጠነው ። የማርያምን ልጅ ይሳንም ግልጽ ታምራትን ሰጠነው በቅዱስ መንፈስ አበረታነው ቁርአኑም ለፊተኞቹ መጽሐፍት አረጋጋጭ ነው ምእራፍ ሁለት ቁጥር 1 ገጽ 9 አንቀጽ 87 እስከ 91 ።

በአራት ህግ እንዲስሩ ቁርአን ምእራፍ 2 አል በቅራህ ክፍል 1 ገጽ 10 አንቀጽ 93 ይናገራል ያዛል ::

ሙሳ ይሳ ነቢያት ሁሉ በተሰጡት የማንለይ ነህ ብለን አመን ምእራፍ 2 አልብቅራህ ክፍል አንድ ገጽ 14 አንቀጽ 136 ::

ወሰን አትለፍ አምላክ ወሰን አላፊን አይወድምና ገጽ 20 ምእራፍ 2 ክፍል 2 አልብቅራህ አንቀጽ 190 ::

የመሪምን ልጅ ይሳንም ግልጽ ታምራትን ሰጠነው በቅዱስ መንፈስ አበረታነው ገጽ 28 ምእራፍ 2 አልብቅራህ ክፍል 3 አንቀጽ 253 ::

በፊት ያሉትን መጽሐፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን መጽሐፉን / ቁርአኑን / ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ :: ተውራትና ወንጀልንም አውርዷል ገጽ 33 ምእራፍ 3 አል ኤምራን ክፍል 3 አንቀጽ 3 ተመልከት ::

መሪም ሆይ አላህ በእርግጥ መረጠሽ አነጻሽም በዓለማት ሴቶች ላይ መረጠሽ :: መሪም ሆይ አላህ ከእርሱ በሆነው ቃል ስሙ አልመሲህ ኢሳ የመሪም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ ከባለሟሎቹ በሆነ ልጅ ያበስርሻል :: ጌታየ ሆይ ሰው ያልነካኝ ስሆን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል አለች :: ነገሩ እንደዚሁ ነው አላህ የሚሻውን ይፈጥራል አንዳችን ባሻ ጊዜ ለእርሱ ይሁን ይለዋል ወዲያውንም ይሆናል አላት :: ጽህፈትንና ጥበብንም ተውራትና ኤንጀልንም ያስተምረዋል ገጽ 37 ምእራፍ 3 አል ኤምራን ክፍል 3 አንቀጽ 42ና 47-48 ይገኛል ::



በነብያት ፈለግ ላይ የመሪምን ልጅ ኢሳን ከተሁራት በስተፊት ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከትለን ኤንጀልንም በውስጡ ቀጥተኛ ብርሀን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቅቆችም መሪና ገሳጭ ሊሆን ሰጠነው :: የኤንጀልንም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ህግ ይፋረዱ አላህ ባወረደው የማይፋረድ እነዛ አመጸኞች ናቸው ገጽ 75ና 76 ምእራፍ 5 ኤል ማኢዳህ ክፍል 6 አንቀጽ 46ና 47 ::

ቅዳሜ ቀን ሰንበት መሆኑን ቁርአን ሲመሰክር ከዛችም በባህሩ ዳርቻ ከነበረችው ከተማ በቅዳሜ ቀን ወሰን ባለፈ ጊዜ በሰንበታቸው ቀን ይላል :: ገጽ 114 ምእራፍ 7 ኤል አአራፍ ክፍል 9 አንቀጽ 163 ተመልከት ::

ዳውድንም ዘብርን ሰተነዋል / ዳዊትንም መዝሙር ሰተነዋል / ገጽ 195 ምእራፍ 17 ኤምራህ ክፍል 15 አንቀጽ 55 ::

የመሪም ልጅ ይሳ በሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው :: ገጽ 211 ምእራፍ 19 መሪም ክፍል 16 አንቀጽ 34 ::

ያችንም አካሏን የጠበቀችውን በሷም ውስጥ ከመንፈሳችን እፍ ያልንባት እርሷንም ልጇንም እንዱሁም ለዓለማት ታምር ያደረግናትን መሪምን አስታውስ :: ይላል ገጽ 217 ምእራፍ 21 ኤል አምቢያ ክፈል 17 አንቀጽ 91 ስለየሱስ አወላለድ ተመልከት :: በተጨማሪም ገብርኤል ለማርያም ስለመውለዷ ባነሳላት ጊዜ በጋብቻ ሰው ያልነካኝ ስሆን አመንዝራም ሳልሆን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች ነገሩ እንደዚሁ ነው

ለስወችም ታምር ከኛም ችሮታ ልናደርገው ይህንን ስራን የተፈረደ ነገር ነው አለና እፍ አለባት ። ወዲያውም እረገዘች ። ገጽ 210 ምእራፍ 19 መሬም ክፍል 16 አንቀጽ 16 - 22 ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የቁርአን ቃል ምስክር በማድረግ እራሳቸውን እያስነበበ እያስተረጎመ እንዲሁም ብዙ መኳንንት ግእዝና አማርኛ አረብኛ አዋቂወች እየተቹበት ጉዳዩ በተጠና ጊዜ ነበር መልኩን ለውጦ ተከሳሽ ትክክለኛ፤ ክሳሽ ጥፋተኛ መሆናቸውን ባለስልጣኖቹ በቀላሉ ተረድተው የሚከተለው የወሰኑት ።

<u>የፍርድ ውሳኔ</u>-

ሃይማኖታችን ለውጣችኋል ስርዓታችንን አፍርሳችኋል እና ቅጣት ተቀብላችሁ ማስተማራችሁን ማቆም አለባችሁ ስትሉ ባቀረባችሁት ክስ የሸህ ዘካርያስ ደረሶች እነ አህመዲንን አቅርበን በሰጡት መልስ እራሳችሁን እያስነበብን እያስተረጎምናችሁ እንዲሁም እያሌ ግእዝና አማርኛ አረብኛም አዋቂወችን ሰብስበን በስፋው ካጠናነው በኋላ እንደተረዳነው ከሆነ ሃይማኖት ለዋጭ ስርእት አፍራሽ ሁናችሁ ያገኘናችሁ እናንተን ስለሆነ አህመዲንና ጓደኞቹ ከሚያስተምሩት ሕግና ስርዓት ጋር በደንብ የተዋወቁ እውነቱን ከሀሰት ለመለየት በእውነተኛ መምህር የታቀዱ ለመምህርነት የተሰጡት ስልጣን ትክክለኛ የሆነ ሁነው ስላገኘናቸው የቀረበባቸው ክስ ውድቅ ሁኖ የጀመሩትን መልካም ተግባር እንዲያክናውኑ በመፋረድ ተስማምተን ወስነናል ። ሲሉ ፈርደው ከሳሽ ተክሳሽን አሰናበቱ ። ከሳሾች ይግባኝ ይሰጠን ብለው ስለጠየቁ ይግባኙ ተሰጣቸው ።



ከሳሾች ከአድዋ ተነስተው በስቆጣ አድርገው ዋግ ሰዩም ኃንጉል የፈረደባቸውን እነ ሸህ አደምን እነሳስተው ጉዞዋቸውን ወደ አዲስ አበባ ሲያመሩ እግረ መንገዳቸው የሆነውን ሁሉ በወሎ ጠቅላይ ግዛት ላገኙት ታላላቅ ሸሆችን እያስረዱ ተጓዙ ።